# ሒሳብ

## የተማሪ መጽሐፍ
## 4ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ውብቱ ጫኔ
ፀጋዬ ሀይሉ
በለጠ ሁሉምታዬ

ገምጋሚዎች

ሙስጠፋ ከድር
ሮዳስ ድሪባ
ገስጥ አሰፋ

ግራፊክስ ዲዛይን

ግርማ ዳርጌ
ኃ/ጊዮርጊስ ተመስገን

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ



አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ



City Government of Addis Ababa
EDUCATION BUREAU

© 2015 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት
የተጠቀመባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣ በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለም ሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን ፣ በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣ በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣ የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ፣ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣ የትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣ የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

City Government of Addis Ababa
EDUCATION BUREAU

ማውጫ ገጽ

ምዕራፍ 1
ሙሉ ቁጥሮች ............................................................... 1
1.1 በ1,000 ፣ 10,000 እና 100,000 መሉ ቁጥሮችን
መቁጠር ............................................................... 1
1.1.1 ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000 እና በ10,000 መቁጠር ................ 1
1.1.2 ሙሉ ቁጥሮችን በ100,000 መቁጠር ................................ 7
1.2 የቁጥር ቤት ዋጋ በባለ 6 እና በላይ ሆሄ ሙሉ
ቁጥሮች ............................................................... 10
1.3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር
እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ............................................ 13
1.4 ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት ................................ 15
1.5 ቁጥሮች ............................................................... 18
1.5.1 የተለያዩ ሀገራት ቁጥሮች ............................................ 19
1.5.2. ከአንድ እስከ መቶ (ወይም ከ ፩-፻) ያሉ
የኢትዮጵያ ቁጥሮች ............................................ 21
1.5.3 ከመቶ (ወይም ከ፻) በላይ ያሉ የኢትዮጵያ
ቁጥሮች ............................................................... 24
የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ ............................................................... 26
የምዕራፍ 1 የማጠቃለያ መልመጃ ............................................ 27
ምዕራፍ 2
እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር እና መቀነስ.......... 30
2.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር............................ 30
2.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ ................................ 36
2.3 መደመርና መቀነስን መሰረት ያደረጉ የቃላት
ፕሮብሌሞችን መፍታት ............................................................... 40
የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ ............................................................... 42
የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ መልመጃ ............................................ 43



The Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

ምዕራፍ 3

እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል........ 44

3.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ................................ 44

3.1.1 የ10,000፣ የ100,000 እና በላይ ብዜቶችን

በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት ................................................ 44

3.1.2 ሙሉ ቁጥሮችን የማባዛት ስልቶች ............................................. 48

3.1.3 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1

ሆሄ እና በ10 ማባዛት ............................................................... 51

3.1.4 እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን

በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት ................................................ 53

3.1.5 ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ

ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት .................................... 54

3.1.6 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን

በባለ 2 እና በላይ ሆሄያቶች ማባዛት .............................................. 62

3.1.7 ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃላት

ፕሮብሌሞችን መፍታት ......................................................... 63

3.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል ................................ 64

3.2.1 እስከ 1,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን

በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማካፈል ............................................... 64

3.2.2 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1

ሆሄ እና በ10 ማካፈል ......................................................... 67

3.2.3 እስከ 100,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1

ሆሄና እና በ10 ማካፈል ........................................................ 69

3.2.4 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1

ሆሄና እና በ10 በቀሪና ያለ ቀሪ ማካፈል ....................................... 71

3.2.5 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 2

እና በላይ ሆሄያት ማካፈል ........................................................ 75

Government of Addis ... EDUCATION BUREAU

3.2.6 ማካፈልን መሰረት ያደረጉ የቃላት

ፕሮብሌሞችን መፍታት ........................................ 76

የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ ........................................ 78

የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ መልመጃ ........................................ 79

ምዕራፍ 4

ክፍልፋዮችና አስርዮሽ ቁጥሮች ........................................ 82

4.1 ክፍልፋዮች የአንድ ሙሉ ነገር ክፍሎች ........................................ 82

4.2 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋዮች

ማወዳደርና በቅደም ተከተላቸው ማስቀመጥ ........................................ 85

4.2.1 ላዕልና ታህት ........................................ 85

4.2.2 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋዮች ማወዳደር ........................................ 87

4.2.3 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋዮች

በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ........................................ 90

4.3 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋይ

መደመርና መቀነስ ........................................ 92

4.3.1 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋይ መደመር........................................ 93

4.3.2 ተመሳሳይ ታህት ያላቸውን ክፍልፋይ መቀነስ ........................................ 94

4.4 አቻ ክፍልፋዮች ........................................ 95

4.5 አስረኛ ፣ መቶኛ እና የአስርሻዊ ቁጥሮች ........................................ 98

4.5.1 አስረኛ እና የአስርሻዊ ቁጥሮች ........................................ 98

4.5.2 መቶኛ እና የአስርሻዊ ቁጥሮች ........................................ 102

4.6 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ የቁጥር ቤቶች ያላቸውን አስርዮሻዊ

ቁጥሮች ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ........................................ 105

4.6.1 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ የቁጥር ቤቶች ያላቸውን

አስርዮሻዊ ቁጥሮች ማወዳደር ........................................ 105

4.6.2 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ ቁጥር ቤቶች ያላቸውን

አስርዮሻዊ ቁጥሮች በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ........................................ 107

4.7 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ ቁጥር ቤቶች ያላቸውን

አስርዮሻዊ ቁጥሮች መደመርና መቀነስ ........................................ 109

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

4.7.1 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ ቁጥር ቤቶች ያላቸውን አስርዮሻዊ ቁጥሮች መደመር ........ 109
4.7.2 እስከ ሁለት አስርዮሻዊ ቁጥር ቤቶች ያላቸውን አስርዮሻዊ ቁጥሮች መቀነስ ........ 111
የምዕራፍ 4 ማጠቃለያ ........ 114
የምዕራፍ 4 የማጠቃለያ መልመጃ ........ 115
ምዕራፍ 5
ጎነ ሶስቶች እና ጎነ አራቶች ........ 117
5.1 በአካባቢያችሁ ያሉ አንግል የሚፈጥሩ ምስሎች ........ 117
5.2 ጎነ ሶስቶች ........ 122
5.2.1 የጎነ ሶስቶች ትርጉም ........ 123
5.2.2 የጎነ ሶስቶች ባህሪያት ........ 124
5.2.3 የጎነ ሶስት አይነቶች ........ 126
5.3 ጎነ አራቶች ........ 130
5.3.1 የጎነ አራቶች ትርጓሜ ........ 130
5.3.2 የጎነ አራት አይነቶችና ባህሪያት ........ 132
የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ ........ 136
የምዕራፍ 5 ማጠቃለያ መልመጃ ........ 138
ምዕራፍ 6
ንድፍ ........ 139
6.1 ተደጋጋሚ ንድፎችን ማጠቃለል ........ 139
6.2 የንደፎች ደንቦች ........ 143
6.3 የንድፎች ተግባራት ........ 146
የምዕራፍ 6 ማጠቃለያ ........ 148
የምዕራፍ 6 የማጠቃለያ መልመጃ ........ 149
ምዕራፍ 7
ልኬት: ርዝመት፣መጠነቁስ እና ይዘት ........ 150
7.1 የርዝመት ልኬትና የምድብ ቅይይር ........ 150

EDUCATION BUREAU

7.1.1 በልኬቶች መካከል ያለ ዝመድና ........ 151
7.1.2 የርዝመት መለኪያ ምድቦችን መደመር እና መቀነስ ........ 153
7.2 የመጠነቁስ ልኬት እና የምድቦች ቅይይር ........ 155
7.3 የይዘት ልኬት እና የምድቦች ቅይይር ........ 159
7.4 የቃላት ፕሮብሌሞች ........ 161
የምዕራፍ 7 ማጠቃለያ ........ 163
የምዕራፍ 7 ማጠቃለያ መልመጃዎች ........ 165
ምዕራፍ 8
መረጃ አያያዝ ........ 166
8.1 መረጃ መሰብሰብ ........ 166
8.2 ባርግራፎችን ማንበብና መግለፅ ........ 169
8.3 መረጃን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞች
ባር ግራፎች እና በአማካኝ መተርጎም ........ 172
የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ ........ 176
የምዕራፍ 8 ማጠቃለያ መልመጃ ........ 177
ምዕራፍ 9
የኢትዮጵያ ጊዜ ........ 179
9.1 ሰዓቶችን፣ ደቂቃዎችን እና ሴኮንዶችን ማንበብ ........ 179
9.2 የጊዜ ምድቦችን ማስላት ........ 181
9.2.1 የጊዜ ምድቦች ዝምድና ........ 181
9.2.2 የጊዜ ምድብን መደመር እና መቀነስ ........ 183
9.3 የጊዜ ምድቦችን ማወዳደር ........ 184
9.4 የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት ........ 185
የምዕራፍ 9 ማጠቃለያ ........ 187
የምዕራፍ 9 ማጠቃለያ መልመጃ ........ 188

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

# ምዕራፍ 1 ሙሉ ቁጥሮች

የመማር ማስተማር ውጤቶች፡- ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ትረዳላችሁ።
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ታወዳድራላችሁ።
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል ታስቀምጣላችሁ።
- ሙሉ ቁጥሮችን መሰረት ያደረገ የዕለት ተዕለት ተግባራዊ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትፈታላችሁ።

## መግቢያ

በሶስተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርታችሁ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል መፃፍ፤ ማስላት፤እንዲሁም ከዕለት ተዕለት ተግባራችሁ ጋር በማገናኘት እንዴት እንደምትጠቀሙ ተምራችኋል። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ፣ በቅደም ተከተል መፃፍ፣ ማወዳደር፣ በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማስቀመጥ፣ ማጠጋጋት፣ የኢትዮጵያና የሌሎች ሀገራት ቁጥሮችን ከማህበራዊ መስተጋብራችሁ ጋር በማገናኘት ትማራላችሁ።

## 1.1 በ1,000 ፣ 10,000 እና 100,000 መሉ ቁጥሮችን መቁጠር

### 1.1.1 ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000 እና በ10,000 መቁጠር

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000 እና በ10,000 መቁጠር



City Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## ተግባር 1:-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት ስሩ

1. ከ0 ጀምሮ 1,000 በመደመር ብትቆጥሩ ከ9,000 ቀጥሎ የምታገኙት ቁጥር ስንት ነው?
2. ከ10,000 በመነሳት በ10,000 ልዩነት እየቆጠራችሁ እስከ 80,000 የምታገኟቸውን ቁጥሮች ዘርዝሩ?
3. በ2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት የተሳተፉ ታዳጊዎችና ወጣቶች ብዛት አንድ ሳምንት ሰማንያ ሺ. ቢሆኑ እና ለ4 ሳምንት በ10,000 ልዩነት እየጨመሩ ቢሳተፉ በ4ኛው ሳምንት የተሳተፉትን በጎ ፈቃደኞች ቁጥር በአሀዝ እና በፊደል በመፃፍ ስንት 1 ሺዎች እና 10 ሺዎች እንዳሉ ዘርዝሩ?

### ማስታወሻ

- በቻርት 1,000 እና 10,000 ብዛቶችን መቁጠር እንችላለን።
  - ✓ የ1,000 ቁጥሮችን ብዛት በመቁጠር 1,000ዎችን መለየት እንችላለን።




Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

1,000
1,000
1,000
1,000
1,000

አምስት ሺዎች 5,000

1,000
1,000
1,000
1,000
1,000
1,000

ስድስት ሺዎች 6,000

➢ የ10,000 ቁጥሮችን ብዛት በመቁጠር 10,000ዎችን መለየት እንችላለን።

10,000

አስር ሺ 10,000

10,000
10,000

ሀያ ሺ 20,000

10,000
10,000
10,000

ሰላሳ ሺ 30,000

1,000
1,000
1,000
1,000

አርባ ሺ 40,000

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

- በቁጥር መስመር
  - ✓ በሌላ መንገድ በቁጥር መስመር ማየት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በቁጥር መስመር ከ 1,000 በመጀመር በ1,000 ልዩነት እስከ 7,000 ያሉትን ማሳየት እንችላለን፡፡




- **በሰንጠረዥ**
  - ✓ **በሰንጠረዥ በ1,000፣ በ10,000 እየጨመርን ስንሄድ**

| ሙሉ ቁጥር | 1,000 በመደመር | 10,000 በመደመር |
|---|---|---|
| **8** | 1,008 | 10,008 |
| **25** | 1,025 | 10,025 |
| **460** | 1,460 | 10,460 |
| **8,900** | 9,900 | 18,900 |
| **72,000** | 73,000 | 82,000 |
| **120,000** | 121,000 | 130,000 |
| **900,000** | 901,000 | 910,000 |

- በቁጥር ቤት
  - ✓ በቁጥር ቤት ዋጋ በ1,000 እና 10,000 መቁጠር እንችላለን፡፡

**ሙሉ ቁጥሮች** በቤት ዋጋ በሰንጠረዥ በቅደም ተከተል ሲቀመጥ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ1 ሚሊዮን ቤት | የ100 ሺ ቤት | የ10 ሺ ቤት | የአንድ ሺ ቤት | የ100 ቤት | የ10 ቤት | የ1 ቤት |

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 1፡-** ከታች የተሰጠውን የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ በመጠቀም ሙሉ ቁጥሮችን በፊደል እና በአሀዝ ፃፉ፡፡

| ተ/ቁ | የሺ ቤት | የመቶ ቤት | የአስር ቤት | የአንድ ቤት |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | 2 | 4 | 1 | 0 |
| ለ | 5 | 3 | 9 | 7 |
| ሐ | 9 | 9 | 9 | 9 |

**መፍትሔ ፡-**

| **በፊደል ሲፃፍ** | **በአሀዝ ሲፃፍ** |
|---|---|
| ሀ. ሁለት ሺ አራት መቶ አስር | 2,410 |
| ለ. አምስት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና ሰባት | 5,397 |
| ሐ. ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ | 9,999 |

**ምሳሌ 2፡-** ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች 1,000፣ 10,000 በመደመር ስትቆጥሩ የሚገኙትን ለዩ?

610,000፣ 820,000፣ 611,000፣ 200,000፣ 612,000፣ 300,000፣ 830,000፣ 400,000፣ 500,000፣ 90,000፣ 840,000፣

**መፍትሔ፡-**

- ✓ በ1,000 ልዩነት፡

  610,000፣ 611,000፣ 612,000፣

- ✓ በ10,000 ልዩነት፡

  820,000፣ 830,000፣ 840,000

**ምሳሌ 3፡-** በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም ውስጥ በየዓመቱ የሚቆጥቡ ግለሰቦች በዓመት ስድስት መቶ አስራ ሁለት ሺ አንድ መቶ አርባ ሰባት ብር ይቆጥባሉ፡፡ ይህንን ቁጥር በአሀዝ በመፃፍ ስንት አንድ ሺዎች እና አስር ሺዎች እንዳሉ ፃፉ

**መፍትሔ፡-**

612,147 ብር = 600,000 +10,000+2,000+100+40+7

1 አስር ሺ እና 2 አንድ ሺዎች አሉ

## መልመጃ 1

1. የሚከተሉትን ቀጣይ ተከታታይ ቁጥሮች በሳጥኑ ውስጥ ፃፉ




2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን ቁጥር ክፍት ቦታዎች ላይ ሙሉ::

   ሀ. 50,000 ፣ ______ ፣ ______ ፣ ______ ፣ 90,000

   ለ. 80 ሺ፣ ________ ፣ ________፣ ______፣ 84 ሺ

3. ከሚከተሉት 50,000 በመደመር ስትቆጥሩ የማይገኙት ቁጥሮች የትኞቹ እንደሆኑ ለዩ?

   60,000፣ 120,000፣ 110,000፣ 20,000፣ 25,000፣ 350,000፣

4. ከ55,000 በመጀመር እስከ 65,000 ድረስ 1,000 በመደመር በመቁጠር ቁጥሮቹን ጻፉ::

5. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማዋን ፅዳትና ውበት ለመጠበቅ በአካባቢ ፅዳትና እንክብካቤ ላይ የተሳተፉ ነዋሪዎች በ5 ዙሮች ቢሳተፉ እና በ1ኛው ዙር 600,000 ቢሆኑና በየዙሩ 50,000 ተሳታፊዎች ቢጨምሩ በ5ኛው ዙር የተሳተፉ ነዋሪዎች ስንት ናቸው?

6. የሚከተለውን የቁጥር መስመር በመመልከት የጎደለውን ሙሉ::



## 1.1.2 ሙሉ ቁጥሮችን በ100,000 መቁጠር

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

❖ ሙሉ ቁጥሮችን ማንበብ እና መፃፍ፡፡

**ተግባር 2**

1. የሚከተሉትን በአሀዝ የተፃፉ ሙሉ ቁጥሮችን በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ. 155,762 ለ. 348,139 ሐ. 420,685 መ. 847,348

2. የሚከተሉትን በፊደል የተፃፉ ሙሉ ቁጥሮችን በአሀዝ ፃፉ፡፡

   ሀ. ስምንት መቶ ሃያ ስምንት ሺ ሰባት መቶ አስራ ዘጠኝ

   ለ. አምስት መቶ ስልሳ ሶስት ሺ አራት መቶ ሰላሳ ስምንት

ማስታወሻ

➢ የ100,000 ቁጥሮችን ብዛት በመቁጠር 100,000ዎችን መለየት እንችላለን፡፡



1. ከ400,000 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች በ100,000 ልዩነት አስቀምጡ::




✓ **በሰንጠረዥ 100,000 እየጨመርን ስንሄድ**

| + | ሙሉ ቁጥር | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 8 | 25 | 460 | 8,900 | 72,000 | 120,000 | 900,000 |
| **100,000 በመደመር** | 100,008 | 100,025 | 100,460 | 108,900 | 172,000 | 220,000 | 1,000,000 |

**ምሳሌ 4** ፡- ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ስንት 100,000ዎች እንዳሉ አብራሩ::

ሀ. 250,000 ለ. 89,000 ሐ. 900,000 መ. 486,000

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 2 መቶ ሺዎች ለ. 0 ሐ. 9 መቶ ሺዎች መ. 4 መቶ ሺዎች

**ምሳሌ 5**፡- ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች 100,000 በመደመር ስትቆጥሩ የሚገኙትን ለዩ

200,000፣ 840,000፣ 300,000፣ 830,000፣ 400,000፣ 500,000፣ 90,000፣

**መፍትሔ፡-**

በ100,000 ልዩነት፡

✓ 200,000፣ 300,000፣ 400,000፣ 500,000

**ምሳሌ 6**፡- ከዚህ በታች በአሀዝ የተዘረዘሩትን ሙሉ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ::

ሀ.10,374 ለ.45,629 ሐ. 99,999 መ.346,821 ሠ.879,562

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**መፍትሔ፡-**

ሀ. አስር ሺ ሶስት መቶ ሰባ አራት

ለ. አርባ አምስት ሺ ስድስት መቶ ሃያ ዘጠኝ

ሐ. ዘጠና ዘጠኝ ሺ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ

መ. ሶስት መቶ አርባ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሃያ አንድ

ሠ. ስምንት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ አምስት መቶ ስልሳ ሁለት

**ምሳሌ 7፡-**ከዚህ በታች በአሀዝ የተዘረዘሩትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ፃፉ፡፡

ሀ. 93,268 ለ. 248,967 ሐ. 864,000

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 93,268 $= 90{,}000 + 3{,}000 + 200 + 60 + 8$

ለ. 248,967 $= 200{,}000 + 40{,}000 + 8{,}000 + 900 + 60 + 7$

ሐ 864,000 $= 800{,}000 + 60{,}000 + 4{,}000 + 0 + 0 + 0$

**ምሳሌ 8** ፡- ቀጥሎ በመተንተን ለቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች የሚወክሏቸውን አሀዝ ፃፉ፡፡

ሀ. $80{,}000 + 2{,}000 + 100 + 50 + 9$

ለ. $300{,}000 + 50{,}000 + 6{,}000 + 700 + 20 + 0$

ሐ. $700{,}000 + 80{,}000 + 9{,}000 + 400 + 60 + 2$

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 82,159 ለ. 356,720 ሐ. 789,462

**ምሳሌ 9፡-**

በአንድ ትምህርት ቤት የሚገኙ መምህራንና ሰራተኞች በ2012 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ታላቁ ህዳሴ ግድብ በገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ በመወያየት የአንድ ወር ደሞዛቸውን ቦንድ ለመግዛት ተስማምተው የዘጠኝ መቶ ሰማንያ አምስት ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ብር ቦንድ ገዙ፡፡ ይህ የተገዛበትን ገንዘብ በአሀዝ ፃፉ፡፡

**መፍትሔ፡- በአሀዝ** ሲፃፍ 985,860 ብር

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

### መልመጃ 2

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ሙሉ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ. 843,976　　ለ. 289,621　　ሐ. 999,901

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በአሀዝ እና በቁጥር ቤት ሰንጠረዥ አስቀምጡ፡፡

   ሀ. ሰማንያ ሁለት ሺ አራት

   ለ. አንድ መቶ አምሳ ዘጠኝ ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ ስምንት

   ሐ. አራት መቶ ሺ አስር

   መ. ስድስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺ አምስት መቶ ሰባ ዘጠኝ

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ግለፁ፡፡

   ሀ. 546,865　　ለ. 368,509　　ሐ. 999,237　　መ. 218,132

4. ቀጥሎ በመተንተን ለቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች የሚወክሏቸውን አሀዝ ጻፉ

   ሀ. $900{,}000 + 80{,}000 + 5{,}000 + 400 + 70 + 5$

   ለ. $300{,}000 + 40{,}000 + 6{,}000 + 400 + 60 + 8$

5. ከ600,000 ጀምሮ እስከ 1,000,000 ድረስ 100,000 በመደመር ቁጥሮቹን በቁጥር መስመር ጻፉ፡፡

## 1.2 የቁጥር ቤት ዋጋ በባለ 6 እና በላይ ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን በቤት ዋጋ ማስቀመጥ

**ተግባር 3**

1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ወስጥ ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮችን ለዩ ፡፡

   ሀ. 895,002　　ለ. 58,695　　ሐ. 85,623　　መ. 125,348

ማስታወሻ

- ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ለማስቀመጥ ከቀኝ ወደ ግራ የ1፣ የ10፣ የ100፣ የ1,000፣ የ10,000 እና የ100,000 ቤት በማለት ማስቀመጥ ይኖርባችኋል፡፡
- የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ የአንድን ቁጥር ሆሄያት የቁጥር ቤት ዋጋ በቀላሉ ለማወቅ እና ለመረዳት ይጠቅማል፡፡
- በተለያዩ የቁጥር ቤት ዋጋ የተፃፉ ቁጥሮች የተለያዩ የቁጥር ቤት ዋጋ ይኖራቸዋል፡፡

...partment of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 10፡-** ከዚህ በታች የተሰጡትን ባለ ስድስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች የእያንዳንዳቸዉን ሆሄያት የቤት ዋጋ ፃፉ።

ሀ. 128,645    ለ. 700,009

**መፍትሔ፡-**




**ሀ.**




**ለ.**

**ምሳሌ 11.** በሙሉ ቁጥር 897,564 ውስጥ ስንት መቶ ሺዎች፣ አስር ሺዎች፣ አንድ ሺዎች፣ መቶዎች፣ አስሮችና አንዶች አሉ?

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**መፍትሔ፡-**




8 መቶ ሺዎች፣ 9 አስር ሺዎች፣ 7 ሺዎች፣ 5 መቶዎች፣ 6 አስሮችና 4 አንዶች አሉ።

**ምሳሌ 12፡-** ከዚህ በታች የተሰጡትን ባለ 6 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት አስቀምጡ።

ሀ. 569,437 ለ. 601,286

**መፍትሔ፡-**




ለ. 601,286



### መልመጃ 3

1. ለሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ከጎን የተሰጡት ቁጥሮች የስንት ቤት ዋጋ እንደሚያመለክቱ ፃፉ፡፡

ሀ. ከሙሉ ቁጥር 867,042 ውስጥ የ8 የቤት ዋጋ ስንት ነው?

ለ. ከሙሉ ቁጥር 658,982 ውስጥ የ5 የቤት ዋጋ ስንት ነው?

ሐ. ከሙሉ ቁጥር 962,423 ውስጥ የ4 የቤት ዋጋ ስንት ነው?

2. በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን መቶ ሺዎች፣ አስር ሺዎች፣ ሺዎች፣ መቶዎች፣ አስሮችና አንዶች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. 469,435 ለ. 301,289 ሐ. 37,645

3. ከዚህ በታች የተሰጡትን ባለ ስድስት ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ሰንጠረዥ አስቀምጡ፡፡

ሀ. 321,465 ለ. 702,386 ሐ. 248,647

## 1.3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደር እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

❖ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማወዳደርና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ

### ተግባር 4፡-

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩባቸዉ ፡፡

1. የሚከተሉትን ጥንድ ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ፡፡

ሀ. 834,028 እና 823,879 ለ. 734,028 እና 734,079

### ማስታወሻ፡-

➢ ሁለት የተለያዩ ሆሄ ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች ሲወዳደሩ ብዙ ሆሄ ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች ትንሽ ሆሄ ካላቸው ሙሉ ቁጥሮች ይበልጣሉ፡፡

➢ ሁለት እኩል ሆሄ ብዛት ያላቸው ሙሉ ቁጥሮች ሲወዳደሩ ከቁጥሮቹ ግራ ጫፍ በመጀመር ወደ ቀኝ በማየት በቁጥር ቤታቸው በማወዳደር ትልቅ ሆሄ ያለው ሙሉ ቁጥር ይበልጣል፡፡



Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 13፡-** የሚከተሉትን ጥንድ ሙሉ ቁጥሮች አወዳድሩ

ሀ. 94,005 እና 940,879 ሐ. 834,082 እና 834,077

ለ. 642,859 እና 642,859 መ. 714,005 እና 914,006

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 94,005 < 940,879 ምክንያቱም ባለ 5 ሆሄ ያንሳል ከባለ 6 ሆሄ ስለሆነ

ለ. 642,859 = 642,859

ሐ. 834,082 > 834,077 ምክንያቱም ባለ 8 > 7፣ የ10 ቤት ሆሄውን በማየት

መ. 714,005 < 914,006 ምክንያቱም 7 < 9፣ የ100,000 ቤት ሆሄውን በማየት

**ምሳሌ 14፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስቀምጡ

ሀ. 846,675፣ 568,489፣ 746,528፣ 823,947፣ 642,251

ለ. 946,674፣ 668,480፣ 546,529፣ 923,942፣ 442,258

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 568,489፣ 642,251፣ 746,528፣ 823,947፣846,675

ለ. 442,258፣ 546,529፣ 668,480፣923,942፣ 946,674

## መልመጃ 4

1. ለሚከተሉት ጥንድ ሙሉ ቁጥሮች የ "<" ፣ ">" ወይም "=" ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ።

   ሀ. 654,126________ 679,368

   ለ. 900,008________900,004

   ሐ. 69,682________694,657

   መ. 328,414___328,413

   ሠ. 592,367___592,367

2. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል ትልቁን እና ትንሹን ቁጥር ለይታችሁ አውጡ።

   ሀ. 646,674፣ 668,480፣ 646,529፣ 623,942፣ 642,258

   ለ. 946,670፣ 946,484፣ 946,525፣ 946,948፣ 946,250

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

3. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

   ሀ. 446,675፣ 568,489፣ 346,528፣ 523,947፣ 442,251

   ለ. 846,674፣ 768,480፣ 946,529፣ 923,842፣ 742,258

   ሐ. 546,875፣ 546,482፣ 546,528፣ 546,247፣ 546,251

4. ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተዘረዘሩትን ሙሉቁጥሮች ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

## 1.4 ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- ሙሉ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸው ማጠጋጋት፡፡

**ተግባር 5፡-**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ

1. የተጠቀሱት ሙሉ ቁጥሮች ወደ የትኛው የ10፣ የ100 እና የ1,000 ብዜት እንደሚጠጋጋ በመለየት ፃፉ

   ሀ 12፣ (10, 20)   ለ 270፣ (200,300)   ሐ 6,990፣ (6,000፣7,000)

2. የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የመማሪያ ክፍላቸውን ፅዳትና ንፅህና ለመጠበቅ ለዚሁ አገልግሎት የሚውል 149 ብር አዋጡ፡፡ የተዋጣው የገንዘብ መጠን ወደ 10 ቤትና ወደ 100 ቤት አጠጋጉ፡፡

**ማስታወሻ**

1. "~" ይህ የአቅራብ ምልክት ነው፡፡ ሲነበብ ይቀርባል ተብሎ ይነበባል፡፡
2. አንድ የተሰጠን ሙሉ ቁጥር ወደ 10 ቤት ለማጠጋጋት
   - የ1 ቤት ሆሄው ከ5 በታች ከሆነ የአንድ ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ10 ቤት ዋጋውን እንዳለ መፃፍ፡፡
   - የ1 ቤት ሆሄው 5 እና በላይ ከሆነ የአንድ ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ10 ቤት ዋጋው ላይ 1 መደመር
3. አንድ የተሰጠን ሙሉ ቁጥር ወደ 100 ቤት ለማጠጋጋት

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

- የ10 ቤት ሆሄው ከ5 በታች ከሆነ የአንድ  እና የ10 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ100 ቤት ዋጋውን እንዳለ መፃፍ፡፡
- የአስር ቤት ሆሄው 5 እና በላይ ከሆነ የአንድ እና የ10 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ100 ቤት ዋጋው ላይ 1 በመደመር

4. አንድ የተሰጠን ሙሉ ቁጥር ወደ 1000 ቤት ለማጠጋጋት
   - የ100 ቤት ሆሄው ከ5 በታች ከሆነ የ1፣ የ10 እና የ100 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ1,000 ቤት ዋጋውን እንዳለ መፃፍ፡፡
   - የ100 ቤት ሆሄው 5 እና በላይ ከሆነ የ1፣ የ10 እና የ100 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ1000 ቤት ዋጋው ላይ 1 መደመር፡፡
5. አንድ የተሰጠን ሙሉ ቁጥር ወደ 10,000 ቤት ለማጠጋጋት
   - የ1000 ቤት ሆሄው ከ5 በታች ከሆነ የ1፣ የ10፣ የ100 እና የ1,000 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ10,000 ቤት ዋጋውን እንዳለ መፃፍ፡፡
   - የ1000 ቤት ሆሄው 5 እና በላይ ከሆነ የ1፣የ10፣የ100 እና የ1,000 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ10,000 ቤት ዋጋው ላይ 1 መደመር፡፡
6. አንድ የተሰጠን ሙሉ ቁጥር ወደ 100,000 ቤት ለማጠጋጋት
   - የ10,000 ቤት ሆሄው ከ5 በታች ከሆነ የ1፣ የ10፣ የ100፣ የ1,000 እና የ10,000 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ100,000 ቤት ዋጋውን እንዳለ መፃፍ፡፡
   - የ10,000 ቤት ሆሄው 5 እና በላይ ከሆነ የ1፣ የ10፣ የ100፣ የ1,000 እና የ10,000 ቤት ሆሄውን 0 ማድረግ እና የ100,000 ቤት ዋጋው ላይ 1 መደመር፡፡

**ምሳሌ 15፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 10 ቤት ሆሄ አጠጋጉ፡፡

ሀ. 83 ለ .47

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 83 → 80

83, የአንድ ቤት ሆሄ 3 ነው፡፡ በመቀጠል $3 < 5$. የአንድ ቤት ሆሄው 0 ይሆናል፡፡

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

ስለዚህ 83 ወደ አስር ቤት ሲጠጋጋ 80 ነው። በምልክት ሲገለፅ 83~80

ለ. 47 በተመሳሳይ 7 > 5, የአንድ ቤት ዋጋው 0 ይሆንና 4 + 1 = 5.

ስለዚህ 50 ይሆናል። በምልክት ሲቀመጥ 47~50

**ምሳሌ 16፡-**

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 100፣ 1,000፣ 10,000 እና 100,000 ቤት ዋጋ አጠጋጉ።

ሀ. 438,659 ለ. 867,421

**መፍትሔ፡-** ከላይ የተቀመጡትን ማስታወሻዎች መነሻ በማድረግ ይሰራል።

| አሀዝ | የሚጠጋጋበት የቤት ዋጋ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 100 | 1,000 | 10,000 | 100,000 |
| **438,659** | 438,700 | 439,000 | 440,000 | 400,000 |
| **867,421** | 867,400 | 867,000 | 870,000 | 900,000 |

### መልመጃ 5

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 10 ቤትና ወደ 100 ቤት ዋጋ አጠጋጉ።

   ሀ. 6,839 ለ. 955 ሐ. 8,462 መ. 18,132

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 1,000 ቤትና ወደ 10,000 ቤት ዋጋ አጠጋጉ።

   ሀ. 46,462 ለ. 68,308 ሐ. 82,645 መ. 28,657

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 100,000 ቤት ዋጋ አጠጋጉ።

   ሀ. 446,067 ለ. 634,365 ሐ. 978,564 መ. 258,798

4. በኢትዮጵያ በየአመቱ የካቲት 23 ቀን በድምቀት ለሚከበረው የጥቁር ህዝቦች ኩራት ለሆነው የአድዋ ድል በዓል ለማክበር የተሳተፉ ሰዎች ቁጥር 153,602 ቢሆን ይህ ቁጥር ወደ 10,000 እና 100,000 ቤት ዋጋ ሲጠጋጋ ስንት ይሆናል?

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## 1.5 ቁጥሮች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- የቁጥሮችን ምንነት መግለጽ
- የተለያዩ አገራት ቁጥሮችን መጻፍ

**ተግባር 6፡-**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ

1. ቁጥር ማለት ምን ማለት ነው?

### ማስታወሻ

- **ቁጥር** ማለት ለመቁጠር ወይም ደግሞ ለመለካት የምንጠቀምበት የሂሳብ ቁስ ነው፡፡

ቁጥሮች አንድን ነገር ለመለየት (ምሳሌ ስልክ ቁጥር)፣ ለመደርደር (መቁጠሪያ ቁጥር)፣ መለያ ለመስጠትእና ለመሳሰሉት ይጠቅማሉ፡፡

- የቁጥር ምልክቶች
  - **የሕንዳዊ – አረባዊ** ቁጥሮች ምልክቶች (0፣ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9) ናቸው፡፡ **ሕንዳዊ-አረባዊ** ቁጥር ምልክት አደረጃጀት፣ በአማርኛ ስሙ ዜሮ፣ አንድ፣ ሁለት ፣ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት እና ዘጠኝ ናቸዉ፡፡
  - የኢትዮጵያ ቁጥሮች የግዕዝ ቁጥሮች ሲሆኑ እነዚህም መሰረታዊ የሚባሉት

    ፩፣ ፪፣ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮፣ ፯፣ ፰፣ ፱፣ ፲፣ ፳፣ ፴፣ ፵፣ ፶፣ ፷፣ ፸፣ ፹፣ ፺ ፣ ፻ ናቸው

### 1.5.1 የተለያዩ ሀገራት ቁጥሮች

ማስታወሻ

1. **የኢትዮጵያ ቁጥሮች፡** የግዕዝ ቁጥሮች ሲሆኑ እነዚህም መሰረታዊ የሚባሉት

   **፩፣ ፪፣ ፫፣ ፬፣ ፭፣ ፮፣ ፯፣ ፰፣ ፱፣ ፲፣ ፳፣ ፴፣ ፵፣ ፶፣ ፷፣ ፸፣ ፹፣ ፺፣ ፻፣ ፼.** ናቸው

በኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር /የቀን መቁጠሪያ/ ላይ የምናገኛቸውን በየወቅቱ የሚከበሩትን ሃይማኖታዊ በዓላትንና ብሔራዊ በዓላትን ለማክበር የምንጠቀመው የቀን አቆጣጠር የግእዝ ቁጥር /ኢትዮጵያዊ/ ቁጥር እንደሆኑ በግልጹ ልንረዳውና ተገቢውን ስያሜ አውቀን በስሙ ልንጠራው ይገባል።

2. ሕንዳዊ-አረባዊ ቁጥሮች በተለምዶ የአረብ ቁጥሮች ሲባሉ መሰረታዊ የሆኑት ከ0 እስከ 9 ያሉት ናቸው። እነዚህም፡-

   **0፣ 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8፣ 9**
3. የሮማውያን ቁጥሮች መሰረታዊ የሆኑት 7 ሲሆኑ ምልክቶቹ I፣ V፣ X፣ L፣ C፣ D እና M ናቸው፣ በቅደም ተከተል ለ1፣ 5፣ 10፣ 50፣ 100፣ 500 እና 1,000 **ሂንዱ-አረብኛ** የቁጥር ስርዓት ናቸው።

በመሰረታዊነት ደረጃ

| ሮማን ቁጥር | የሚወክለው የሂንዱ አረቢክ ቁጥር |
|---|---|
| I | 1 |
| V | 5 |
| X | 10 |
| L | 50 |
| C | 100 |
| D | 500 |
| M | 1000 |

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

እነዚህ ሲሆኑ ከነዚህ ምልክቶች ያነሱት በግራ ሲሆኑ መቀነስ በቀኝ ሲሆኑ መደመር ይሆናል። ለምሳሌ ምልክት ከሌላው እኩል ወይም የበለጠ እሴት በኋላ የተቀመጠው ዋጋውን ይጨምራል; ለምሳሌ II = 2 እና LX = 60

ከአንድ ትልቅ እሴት በፊት የተቀመጠው ምልክት ዋጋውን ይቀንሳል; ለምሳሌ IV = 4, XL = 40 እና CD = 400. በአንድ ቁጥር ላይ የተቀመጠ ባር ዋጋውን በ1,000 ያባዛል። እነዚህ ቅርጾች እንደ ላቲን ሆሄያት I, V, X, L, C, D, M ለመምሰል የጀመሩ ከ1 ዓ.ዓ አካባቢ ነው።

የሮማውያን ቁጥሮች ገበታ ከሂንዱ-አረብ ጋር ያላቸው ዝምድና

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 = I | 10 = X | 100 = C | |
| 2 = II | 20 = XX | 200 = CC | |
| 3 = III | 30 = XXX | 300 = CCC | |
| 4 = IV | 40 = XL | 400 = CD | |
| 5 = V | 50 = L | 500 = D | |
| 6 = VI | 60 = LX | 600 = DC | |
| 7 = VII | 70 = LXX | 700 = DCC | 1000 = M |
| 8 = VIII | 80 = LXXX | 800 = DCCC | 2000 = MM |
| 9 = IX | 90 = XC | 900 = CM | 3000 = MMM |

እያለ ይቀጥላል።

**ምሳሌ 17**፡- የሚከተሉትን ቁጥሮች የሚወክሏቸውን አሀዝ በፊደል ፃፉ

ሀ. LXXX ለ.. D ሐ. MMM መ. ፸፬፻፯

**መፍትሔ** ፡-

ሀ. LXXX = ሰማንያ ለ .D = አምስት መቶ ሐ. MMM = ሶስት ሺ

መ. ፸፬፻፯ = ሰባት ሺ አራት መቶ ሰባት (7407)

**መልመጃ 6**

1. የተለያዩ አገራት ቁጥሮችን ቢያንስ 5 ዘርዝሩ።
2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በፊደል ፃፉ

ሀ. DM ለ. CD ሐ. MM

መ. ፸፯፻፬ ሠ. ፺፬፻፺፬ ረ. ፶፫፻

## 1.5.2. ከአንድ እስከ መቶ (ወይም ከ ፩–፻) ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃቶች**

- ከ1 እስከ 100 ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን መለየት፡፡
- ከ1 እስከ 100 ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን መፃፍ፡፡
- ከ1 እስከ 100 ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን ማወቅ፡፡

### መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያ የተለያዩ ታሪኮች፣ ባህሎች፣ ቋንቋዎች፣ እምነቶች፣ ወጎችና ሌሎችም በርካታ መለያዎች ያሏት፣ የራስዋ የሆነ ፊደል፣ ቁጥር፣ የቀን አቆጣጠር፣ የጥንታዊ የሰው ልጅ መገኛ እና የጥንታዊ ጀግኖች አባቶቻችን አገር፣ ተደጋግፈውና ተረዳድተው የሚኖሩ የታታሪና የቅን ህዝቦች መኖሪያ፣ መልካም እና ተስማሚ የአየር ንብረት ባለቤት ናት፡፡

የግእዝ ቋንቋ ጥንታዊያን ከተሰኙ ቋንቋዎች መካከል አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በቀን አቆጣጠርና በሥነ ጽሑፎቻቸው ሲጠቀሙበት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ቆይቷል፡፡ ዛሬም የግእዝ ቁጥሮች በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ ሥፍራ አላቸው፡፡

ኢትዮጵያ አገራችን የራስዋ የሆነ ቁጥር ይኑራት እንጅ በአግባቡ አልተጠቀመችበትም፡፡ ተማሪዎችም ስለዚህ ቁጥሮች በቂ እውቀትና ግንዛቤ የላቸውም፡፡ በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ ስለ ታሪካዊቷ ኢትዮጵያ ቁጥሮች ትማራላችሁ፡፡

### 1.5.1.1 መሰረታዊ የኢትዮጵያ ቁጥሮች

**ተግባር 7**

በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመስራት መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. አሁን የምንጠቀምንባቸው ቁጥሮች የማን አገር ቁጥሮች ናቸው?
2. ከምታውቋቸው የኢትዮጵያ ቁጥሮች መካከል 5ቱን ዘርዝሩ፡፡
3. ከዚህ በታች የተሰጡትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. ፩ ለ. ፫ ሐ. ፱ መ. ፲ ሠ. ፴ ረ. ፻

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## ማስታወሻ

➢ ከኢትዮጵያ ቁጥሮች መካከል መሰረታዊ ቁጥሮች የሚባሉት (፲፱) ናቸው።

እነርሱም፡-

| ግዕዝ | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አረቢክ** | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 |

➢ መሰረታዊ ቁጥሮችን በመጠቀም ሌሎች ቁጥሮችን በቀላሉ ማንበብና መፃፍ እንችላለን። ይኸውም

| ተ/ቁ | ከ እስከ | በ10 ቤት ሆሄው መፃፍ ያለብን ቁጥር |
|---|---|---|
| ፩ | 11–19 | ፲፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፪ | 21–29 | ፳፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፫ | 31–39 | ፴፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፬ | 41–49 | ፵፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፭ | 51–59 | ፶፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፮ | 61–69 | ፷፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፯ | 71–79 | ፸፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፰ | 81–89 | ፹፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |
| ፱ | 91–99 | ፺፡ በመቀጠል በቀኝ በኩል የአንድ ቤት ሆሄውን መፃፍ |

**ምሳሌ 18 ፡-**

ከዚህ በታች በአሀዝ የተፃፉትን ሙሉ ቁጥሮች በኢትዮጵያ ቁጥሮች ፃፉ።

ሀ. 33 ለ. 56 ሐ. 74 መ. 97

**መፍትሔ ፡-**

ሀ. 33ን በኢትዮጵያ ቁጥር ለመፃፍ በመጀመሪያ በ10 ቤት ሆሄ ቦታ ፴ን እንፅፋለን። በመቀጠል በ1 ቤት ሆሄ ቦታ ፫ን እንፅፋለን።

ስለዚህ 33 በኢትዮጵያ ቁጥር ሲፃፍ **፴፫** ይሆናል።

ለ. 56ን በኢትዮጵያ ቁጥር ለመፃፍ በተመሳሳይ ስልት **፶፮** ይሆናል።

ሐ. 74ን በኢትዮጵያ ቁጥር ለመፃፍ በተመሳሳይ ስልት ፸፬ ይሆናል፡፡

መ 97ን ኢትዮጵያ ቁጥር ለመፃፍ በተመሳሳይ አፃፃፍ ስልት ፺፯ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ 19፡-** ከዚህ በታች የተሰጡትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. ፹፪ ለ. ፸፭ ሐ. ፷፫ መ .፵፬ ሠ. ፺፭ ረ. ፴፮

**መፍትሔ፡-**

ሀ. ሰማንያ ሁለት

ለ. ሰባ አምስት

ሐ. ስልሳ ሶስት

መ. አርባ አራት

ሠ. ዘጠና አምስት

ረ. ሰላሳ ስድስት

## መልመጃ 7

1. የሚከተሉትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ

   ሀ. ፲፬ ለ. ፳፫ ሐ. ፴፮ መ. ፵፬ ሠ. ፶፫

   ረ. ፳፮ ሰ. ፸፯ ሸ .፹፰ ቀ. ፺፱

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በኢትዮጵያ ቁጥሮች ፃፉ

   ሀ. ዘጠና አንድ

   ለ. ሰማንያ ሁለት

   ሐ. ሰባ ሶስት

   መ. ስልሳ አራት

   ሠ. አምሳ ስድስት

   ረ. አርባ አምስት

   ሰ. ሰላሳ አንድ

   ሸ. ሃያ ሶስት

   ቀ. አስራ ሁለት

   በ. አንድ መቶ

3. በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ወጣቶች አንድ አቅመ ደካማ ግለሰብ ለመርዳት በየቀኑ ዘጠና ስምንት ብር ቢያዋጡ በሳ ፈቃደኛ ወጣቶቹ በአንድ ቀን ያዋጡትን የገንዘብ መጠን በኢትዮጵያ ቁጥር ፃፉ፡፡

EDUCATION

## 1.5.3 ከመቶ (ወይም ከ፻) በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮች

### 1.5.3.1. መሰረታዊ ከመቶ በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮች

**ተግባር 8**

በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመስራት መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. ከመቶ በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን ቢያንስ 4ቱን ዘርዝሩ፡፡
2. ከዚህ በታች የተሰጡትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. ፱፻ ለ. ፭፻ ሐ. ፲፻ መ.፻፻ ሠ. ፹፻

**ማስታወሻ**

- ከመቶ በላይ ያሉ የኢትዮጵያ ቁጥሮችን ለመረዳት መሰረታዊ ቁጥሮች የሚባሉት (፲፱) ናቸው፡፡

እነርሱም፡-

| ግዕዝ | ፩ | ፪ | ፫ | ፬ | ፭ | ፮ | ፯ | ፰ | ፱ | ፲ | ፳ | ፴ | ፵ | ፶ | ፷ | ፸ | ፹ | ፺ | ፻ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አረቢክ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 |

- መሰረታዊ ቁጥሮችን በመጠቀም ሌሎች ቁጥሮችን በቀላሉ ማንበብና መፃፍ እንችላለን፡፡ ይኸውም ከ፩ እስከ ፲ በመጠቀም ከፊት ለፊት ፻ በማስቀመጥ መፃፍ ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ፪፻፣ ፫፻፣ ፬፻፣ ፭፻፣ ፮፻፣ ፯፻፣ ፰፻ ፱፻፣ ፲፻፣ ፲፩፻ ...

- 9,099 ለመፃፍ በመጀመሪያ ፺፣ ፻፣ ፺፣ ፱ እናስቀምጣለን፤ ስለዚህ ፺፻፺ ፱ ይሆናል፡፡

**ምሳሌ 20፡-** ከዚህ በታች የተሰጡትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. ፪፻ ለ. ፭፻ ሐ. ፰፻ መ. ፵፻ ሠ. ፺፻

**መፍትሔ፡-**

ሀ. ሁለት መቶ
ለ. አምስት መቶ
ሐ. ስምንት ሺ
መ. አራት ሺ
ሠ. ዘጠኝ ሺ

## መልመጃ 8

1. የሚከተሉትን የኢትዮጵያ ቁጥሮች በፊደል ፃፉ

ሀ. ፲፻ ለ. ፳፻ ሐ. ፴፻ መ. ፬፻ ረ. ፷፻

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች በኢትዮጵያ ቁጥሮች ፃፉ

ሀ. አስር ሺ
ለ. ሰባ ሺ
ሐ. ስድስት ሺ
መ. አራት ሺ አንድ መቶ ሰባ
ሠ. ስምንት ሺ ሁለት መቶ ሰላሳ
ረ. ሁለት ሺ ሰላሳ ስምንት

## የምዕራፍ 1 ማጠቃለያ

- ቁጥሮችን በምናነብበት ጊዜ ከቀኝ ወደ ግራ የአንድ ቤት፣ የአስር ቤት፣ የመቶ ቤት እያልን እስከ ቁጥሩ መጨረሻ እናነባለን፡፡
- ሁለት ሙሉ ቁጥሮችን ለማወዳደር ከግራ ወደ ቀኝ በመጀመር እናወዳድራለን፡፡ ሆሄያቱ እኩል ካልሆኑ ትልቅ ሆሄያት ያለው ይበልጣል፡፡
- ሙሉ ቁጥሮችን ለማጠጋጋት ከሚጠጋጋበት ቤት በስተቀኝ የሚገኘው ሆሄ አምስት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ወደ ላይ ይጠጋጋል፡፡ ነገርግን ከአምስት በታች ከሆነ ወደ 0 ይጠጋጋል፡፡
- **ቁጥር** ፦ ለመቁጠር ወይም ደግሞ ለመለካት የምንጠቀምበት የሂሳብ ቁስ ነው፡፡
- የተለያዩ አገራት ቁጥሮች ማለትም **የኢትዮጵያ** ቁጥሮች፡ የግዕዝ ቁጥሮች፣ **ሕንዳዊ-አረባዊ** ቁጥሮች፣ **የሮማውያን** ቁጥሮች እና ሌሎችም
- ከኢትዮጵያ ቁጥሮች መካከል መሰረታዊ ቁጥሮች የሚባሉት (፲፱) ናቸው፡፡

## የምዕራፍ 1 የማጠቃለያ መልመጃ

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ዓ.ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" እና ዓ.ነገሩ ትክክል ካልሆነ "ሀሰት" በማለት መልሱ፡፡

   ሀ. 100,000 ሙሉ ቁጥርን በ10,000 እና በ1,000 መቁጠር ይቻላል፡፡

   ለ. ሰባ ዘጠኝ በኢትዮጵያ ቁጥር ሲፃፍ ፸፱ ነው፡፡

   ሐ. M፣ ፻፻ እና 1000 እኩል የቁጥር ዋጋ አላቸው፡፡

   መ. በ845, 237 ቁጥር 4 የ1,000 ቤት ነው፡፡

   ሠ. 700,000 + 80,000 + 2,000 + 400 + 70 + 9 የሚወክለው ሙሉ ቁጥር 782,479 ነው፡፡

   ረ. 950,000 በ941,000 እና በ999,000 መካከል የሚገኝ ሙሉ ቁጥሮችን በ10,000 ልዩነት የሚገኝ ነው፡፡

   ሰ. ፳፬ መሰረታዊ የኢትዮጵያ ቁጥር ከሚባሉት ውስጥ ይመደባል፡፡

2. በ12,640 እና በ18,308 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በ1,000 ልዩነት ዘርዝሩ፡፡

3. በ35,690 እናበ 99,816 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በ10,000 ልዩነት ዘርዝሩ፡፡

4. በ237,320 እና በ637,629 መካከል የሚገኙ ሙሉ ቁጥሮችን በ100,000 ልዩነት ዘርዝሩ፡፡

5. ከዚህ በታች በአሀዝ የተዘረዘሩ ሙሉ ቁጥሮችን በፊደል ፃፉ፡፡

   ሀ. 25,809 ለ. 378,006 ሐ. 846,908 መ. 1,000,000

6. ቀጥሎ የቀረቡትን በፊደል የተዘረዘሩ ሙሉ ቁጥሮችን በአሀዝ ፃፉ፡፡

   ሀ. ዘጠኝ መቶ ዘጠኝ ሺ ሶስት

   ለ. አምስት መቶ አርባ ሺ ስድሳ አራት

   ሐ. አንድ መቶ አስር ሺ አንድ

   መ. ሰባት መቶ ሺ ሁለት

7. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች የቁጥር ቤት ሰንጠረዥ በመጠቀም ፃፉ፡፡

   ሀ. 35,804 ለ. 278,153 ሐ. 446,998 መ. 100,012

8. ለሚከተሉት ጥንድ ሙሉ ቁጥሮች የ "<" ">" ወይም "=" ምልክት በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. 584,126_____579,368　　　መ. 828,414___828,414

ለ. 800,001_____800,004　　　ሠ. 792,466_____792,366

ሐ. 99,682_____994,657

9. ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ሙሉ ቁጥሮች ከትንሹ ወደ ትልቁ በቅደም ተከተል ፃፉ፡፡

ሀ. 246,675፣ 568,489፣ 346,525፣ 723,947፣ 442,253

ለ. 446,674፣ 868,480፣ 746,524፣ 923,842፣ 642,252

ሐ. 746,878፣ 546,882፣ 946,528፣ 646,249፣ 346,255

መ. 946,875፣ 946,481፣ 946,524፣ 946,247፣ 946,258

10. በተራ ቁጥር 9 የተዘረዘሩትን ሙሉ ቁጥሮች ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

11. ከዚህ በታች በአሀዝ የተፃፉትን ሙሉ ቁጥሮች በኢትዮጵያ ቁጥሮች ፃፉ፡፡

ሀ. 9　　ለ. 16　　ሐ. 23　　መ. 38

ሠ. 42　　ሰ. 57　　ሸ. 94　　ቀ.81

12. የሚከተሉትን የተለያዩ አገራት ቁጥሮች በፊደል ፃፉ፡፡

ሀ. IV　　ለ. ፲፰　　ሐ. ፵፰　　መ. ፷፬　　ሠ. ፯

13. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ወደ 10፣ 100፣ 1,000፣10,000 እና 100,000 ቤት ዋጋ አጠጋጉ፡፡

ሀ 8,849　　ሐ 765　　ሠ 68,462

ለ 4,397　　መ 45,638　　ረ 582,745

14. በሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ያሉትን መቶ ሺዎች፣ አስር ሺዎች፣ አንድ ሺዎች፣ መቶዎች፣ አስሮችና አንዶች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ሀ. 769,431　　ለ. 801,209　　ሐ. 937,645　　መ. 893　　ሠ. 1,897

15. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በመተንተን ግለፁ፡፡

ሀ. 146,867　　ለ. 428,506　　ሐ. 899,253　　መ. 918,532

16. ቀጥሎ በመተንተን ለቀረቡት ሙሉ ቁጥሮች የሚወክላቸውን በአሀዝ

እና በቁጥር ቤት ሰንጠረዥ ፃፉ፡፡

ሀ. $80,000 + 7,000 + 700 + 40 + 3$

ለ. $900,000 + 40,000 + 4,000 + 200 + 20 + 2$

ሐ. $700,000 + 80,000 + 2,000 + 400 + 70 + 9$

መ. $100,000 + 40,000 + 1,000 + 400 + 60 + 4$

17. በ2012 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኘውን የአንድነት ፓርክ የጎበኙ የተማሪዎች ቁጥር በጥር ወር 9,987 እንዲሁም በመጋቢት ወር 9,898 ቢሆኑ በየትኛው ወር ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጎብኚ ተመዘገበ?

18. አገራችን ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በተለያዩ አካባቢዎች የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ታካሒዳለች፡፡ በመሆኑም በ2012 ዓ.ም በነበረው መርሀ ግብር በ1ኛው ዙር 90,000፣ በ2ኛው ዙር 95,000 እና በ3ኛው ዙር 500,000 ችግኞች ቢተከሉ በ100,000 የሚቆጠሩ ችግኞች የተተከሉት በየትኛው ዙር ነው?



Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

# ምዕራፍ 2 እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመር እና መቀነስ

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡ ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር፣ መቀነስ ትችላላችሁ፡፡
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መሰረት ያደረጉ መደመርና መቀነስ በመተግበር ትሰራላችሁ፡፡

**መግቢያ**

በሶስተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርታችሁ እስከ 10,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር እና መቀነስ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመርና መቀነስ ትማራላችሁ፡፡

## 2.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

**የንዑስ ርእስ የመማር ብቃት**

- **እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር**

**ተግባር 1**

ጥያቄዎችን በቡድን በመሆን ከተወያያችሁባቸው በኋላ መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 4,672+1,000 ለ. 856,724+34,577

**ምሳሌ** 1፡- የሚከተሉትን ቁጥሮች በመነጣጠል ደምሩ፡፡

ሀ. 7+9 ለ. 12+ 9 ሐ. 14 + 8

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**መፍትሔ፡-** ከሌላው ላይ በመቀነስ እና በመደመር 10 እንዲመጣ ማድረግ

ሀ. 7+9
= 6+1+9
=6+10=16

ለ. 12+ 9
= 11+1+9
= 11+10= 21

ሐ. 14 + 8
= 12+2+8
= 12+10= 22

**ምሳሌ** 2 አስሮችን እና አንዶችን በማጣመር የሚከተሉትን ደምሩ፡፡

ሀ. 56 + 48 ለ. 97 + 68

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 56 + 48
= 50+6+40+8
= 50+40+14
= 90+10 +4
= 104

ለ. 97 + 68
= 90 + 7 + 60 + 8
= 90 + 60 + 8 +7
= 150 + 8 + 2 + 5
= 150 +10 +5
= 160 + 5 = 165

**ምሳሌ** 3 የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ደምሩ፡፡

ሀ. 358 + 459 ለ. 2,366 + 945 ሐ. 156,760 + 24,816

**መፍትሔ፡-**

መጀመሪያ 10፣ 100፣ 1000፣ 10,000 እና 100,000 ብዜት በመተንተን

ሀ. 358 + 459
= 300 + 50 + 8 + 400 + 50 + 9
= 700+100+17
= 700 + 100 + 10 + 7
= 810 + 7
= 817

ለ. 2,366 + 945
= 2,000 + 300 + 60 + 6 + 900 + 40 + 5
= 2,000 + 1200 +100 + 11
= 2,000 +1300 +11
= 3,300 +11
= 3,311

ሐ. 156,760 + 24,816
= 100,000 + 50,000 + 6,000 + 700 + 60 + 20,000 + 4,000 + 800 + 10 + 6
= 100,000 + 50,000 + 20,000 + 4,000 + 6,000 + 700 + 800 + 60 + 10 + 6
=181,576

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

# ያለ አለኝታ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር

## ማስታወሻ

➢ ሙሉ ቁጥሮችን ለመደመር መጀመሪያ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቁልቁል በማስቀመጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ እየደመርን መሄድ ይኖርብናል፡፡

ምሳሌ 4 ፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ በማስቀመጥ ድምራቸዉን ፈልጉ፡፡

ሀ. 326 + 73 ሐ. 3,562 + 2,314

ለ. 515 + 272 መ. 331,256 + 42,513

**መፍትሔ፡-**

ሀ.

| | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት |
|---|---|---|---|
| | 3 | 2 | 6 |
| + | ↓ | 7 | 3 |
| = | 3 | 9 | 9 |

ስለዚህ 326 + 73 = 399 ይሆናል፡፡

ለ.

| | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት |
|---|---|---|---|
| | 5 | 1 | 5 |
| + | 2 | 7 | 2 |
| = | 7 | 8 | 7 |

ስለዚህ 515 + 272 = 787 ይሆናል፡፡

ሐ.

| | 1000 ቤት | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት |
|---|---|---|---|---|
| | 3 | 5 | 6 | 2 |
| + | 2 | 3 | 1 | 4 |
| = | 5 | 8 | 7 | 6 |

ስለዚህ 3,562 + 2,314 = 5,876 ይሆናል፡፡

መ.

| | የ100,000 ቤት | 10,000 ቤት | 1000 ቤት | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | 3 | 3 | 1 | 2 | 5 | 6 |
| + | | 4 | 2 | 5 | 1 | 3 |
| = | 3 | 7 | 3 | 7 | 6 | 9 |

ስለዚህ 331,256 + 42,513 = 373,769 ይሆናል፡፡

EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ** 5 የሚከተሉትን በቤት ዋጋቸዉ በማስቀመጥ ቁልቁል ደምሩ፡፡

ሀ. 467,224 + 100,000 ለ. 344,321+650,000

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 467,224 ስለዚህ 467,224 እና 100,000 ተደማሪዎች ሲባሉ
+100,000 567,224 ደግሞ ድምር ይባላል፡፡
= 567,224

ለ. 344,321 ስለዚህ 344,321 እና 650,000 ተደማሪዎች ሲባሉ
+ 650,000 994,321 ደግሞ ድምር ይባላል፡፡
= 994,321

**አስተዉሉ፡-**

- በማንኛዉም ሙሉ ቁጥር ላይ ዜሮ (0) ስንደምር የምናገኘዉ እራሱን ቁጥሩን ነዉ፡፡ ለማንኛዉም ሙሉ ቁጥር ሀ፡- ሀ + 0 = ሀ ይሆናል፡፡

## *በአለኝታ ሙሉ ቁጥሮችን መደመር*

**ማስታወሻ፡**

- ሙሉ ቁጥሮችን ለመደመር መጀመሪያ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቁልቁል በማስቀመጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ አለኝን ወደ ሚቀጥለው የቁጥር ቤት በመውሰድ እየደመርን መሄድ ይኖርብናል፡፡

**ምሳሌ** 6፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ቁልቁል ደምሩ፡፡

ሀ. 689 + 346 ለ. 23,469 + 7,458

ሐ. 453,086 + 382,509 መ. 569,974 + 430,026

**መፍትሔ፡-**

ሀ.

| አለኝ | +1 | +1 | | |
|---|---|---|---|---|
| | 6 | 8 | 9 | ተደማሪ |
| + | 3 | 4 | 6 | ተደማሪ |
| = | 10 | 3 | 5 | ድምር |

ስለዚህ 689+346=1,035 ይሆናል፡፡

ለ.

| አለኝ | +1 | | +1 | +1 | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2 | 3 | 4 | 6 | 9 |
| + | | 7 | 4 | 5 | 8 |
| = | 3 | 0 | 9 | 2 | 7 |

ስለዚህ 23,469 + 7,458 = 30,927 ይሆናል፡፡

ሐ.

| አለኝ | +1 | +1 | | | +1 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4 | 5 | 3 | 0 | 8 | 6 | ተደማሪ |
| + | 3 | 8 | 2 | 5 | 0 | 9 | ተደማሪ |
| = | 8 | 3 | 5 | 5 | 9 | 5 | ድምር |

ስለዚህ 453,086 + 382,509 = 835,595 ይሆናል፡፡

መ.

| አለኝ | +1 | +1 | +1 | +1 | +1 | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | 6 | 9 | 9 | 7 | 4 | ተደማሪ |
| + | 4 | 3 | 0 | 0 | 2 | 6 | ተደማሪ |
| = | 10 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | ድምር |

ስለዚህ 569,974 + 430,026 = 1,000,000 ይሆናል፡፡

## የመደመር የቅይይር ባህርይ እና የተጣማጅ ባህርይ

**ማስታወሻ**

- ለማንኛውም ሙሉ ቁጥሮች ሀ፣ ለ እና መ
  - ✓ ሀ+ለ = ለ+ሀ የመደመር የቅይይር ባህርይ ይባላል፡፡
  - ✓ (ሀ+ለ)+መ = ሀ+(ለ+መ) የመደመር የተጣማጅ ባህርይ ይባላል፡፡

**ምሳሌ 7፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች የመደመር ባህርያቶችን በመጠቀም ደምሩ፡፡

ሀ (20 + 500) + 30 እና 20 + (500 + 30)

ለ 500+300 እና 300+500

Addis Ababa Education Bureau

**መፍትሔ ፡-**

ሀ. (20 + 500) + 30 እና 20 + (500 + 30)

መጀመሪያ ቅንፍ ዉስጥ ያለውን መስራት

(20 +500)+30 = 520 + 30 = 550 እንዲሁም ፡-

20 + (500 + 30) = 20 + 530 = 550 ይህ የመደመር የተጣማጅ ባህሪ ይባላል፡፡

ለ. 500+300 እና 300+500

500+300 = 300+500 = 800 ይህ የመደመር የቅይይር ባህሪ ይባላል፡፡

## መልመጃ 3

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች በመነጣጠል ደምሩ፡፡

   ሀ. 12 + 4  ለ. 8 + 9  ሐ. 14 + 5

2. አስሮች እና አንዶችን በመደመር እና በማጣመር የሚከትሉትን ደምሩ፡፡

   ሀ. 64 + 28  ለ. 57 + 93  ሐ. 75 + 84

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ደምሩ፡፡

   ሀ. 951 + 850  ለ. 3,261 + 6,845  ሐ. 216,760 + 64,412

4. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ በማስቀመጥ ድምራቸዉን ፈልጉ፡፡

   ሀ. 376 + 622  ለ. 6,562 + 5,354

   ሐ. 631,286 + 331,989  መ. 821,286 + 127,579

5. ሰንጠረዡን በትክክለኛዉ መልስ ሙሉ፡፡

| ሀ | ለ | ሀ+ለ | ለ+ሀ |
|---|---|---|---|
| **100,000** | | | 130,000 |
| | 366,657 | 933,379 | |

Addis Ababa City Administration Education Bureau

## 2.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮች መቀነስ

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- **እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ**

**ተግባር 2**

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ቀንሱ፡፡

   ሀ. 6,321 – 340 ለ. 547,389 – 64,278

**ማስታወሻ**

- መ፣ ወ እና ለ ሙሉ ቁጥሮች ቢሆኑ በ መ – ወ = ለ ውስጥ መ ዋና ወ ተቀናሽ ሲሆኑ ለ ደግሞ ልዩነት ይባላል፡፡
- መ – ወ = ለ እውነት ከሆነ መ = ለ + ወ እውነት ነው፡፡ የመቀነስ ውጤትም በመደመር ይረጋገጣል ፡፡

### ያለ ብድር ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**ማስታወሻ**

- ሙሉ ቁጥሮችን ለመቀነስ መጀመሪያ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቁልቁል በማስቀመጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ እየቀነስን መሄድ ይኖርብናል፡፡

**ምሳሌ 8 ፦** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ቀንሱ፡፡ ዋናውን፣ ተቀናሹን እና ልዩነቱን ለዩ፡፡

ሀ. 399 – 75 ለ. 10,366 – 2,315

Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**መፍትሔ፡-**

መጀመሪያ ሙሉ ቁጥሮቹን 10፣ 100፣ 1000፣ 10,000 እና 100,000 ብዜት በመጠቀም መተንተን

ሀ. $399 - 75$

$= 300 + 99 - 70 - 5$

$= 300 + 29 - 5$

$= 300 + 24 = 324$

ስለዚህ 399 ዋና፣ 75 ተቀናሽ እና 324 ደግሞ ልዩነት ይባላሉ፡፡

**ማረጋገጫ** ዋና= ተቀናሽ + ልዩነት

ለ. $10,366 - 2,315 = 10,000 + 300 + 60 + 6 - 2,000 - 300 - 10 - 5$

$= 10,000 - 2,000 + 300 - 300 + 60 - 10 + 6 -$

$= 8,000 + 50 + 1 = 8,051$

**ማረጋገጫ** ዋና = ተቀናሽ + ልዩነት

ስለዚህ 10,366 ዋና፣ 2,315 ተቀናሽ እና 8,051ደግሞ ልዩነት ይባላል፡፡

**ምሳሌ 11**፡-የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቀንሱ፡፡

ሀ. 495—332 ለ. 458,379– 38,254

**መፍትሔ፡-** በመጀመሪያ በየቁጥር ቤት ዋጋቸዉ መፃፍ እና መቀነስ

ሀ.

| | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት | |
|---|---|---|---|---|
| | 4 | 9 | 5 | ዋና |
| – | 3 | 3 | 2 | ተቀናሽ |
| = | 1 | 6 | 3 | ልዩነት |

ስለዚህ 495 – 332 = 163 ይሆናል፡፡

ለ.

| | የ100,000 ቤት | 10,000 ቤት | 1000 ቤት | የ100ቤት | የ10ቤት | የ1ቤት | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 4 | 5 | 8 | 3 | 7 | 9 | ዋና |
| – | | 3 | 8 | 2 | 5 | 4 | ተቀናሽ |
| = | 4 | 2 | 0 | 1 | 2 | 5 | ልዩነት |

ስለዚህ 458,379 – 38,254=420,125 ይሆናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርት ቢሮ
Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## በብድር ሙሉ ቁጥሮችን መቀነስ

**ማስታወሻ፡**

- ሙሉ ቁጥሮችን ለመቀነስ መጀመሪያ ቁጥሮችን በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቁልቁል በማስቀመጥ ከቀኝ በመጀመር ወደ ግራ የተቀናሹ ሆሄ የማይችል ከሆነ ከሚቀጥለዉ ቤት ሆሄ ላይ 1 በመበደር እየቀነስን መሄድ ይኖርብናል፡፡

**ምሳሌ** 10፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ትይዩ በማስቀመጥ ቀንሱ፡፡

ሀ. 585 – 69 ለ. 13,648 – 6,729

ሐ. 578,430 – 269,121 መ. 428,295 – 97,316

**መፍትሔ**፡- በመጀመሪያ በየቁጥር ቤት ዋጋቸዉ ቁልቁል መፃፍ እና መቀነስ

| ሀ. | | 7 | 15 | |
|---|---|---|---|---|
| | 5 | ~~8~~ | ~~5~~ | ዋና |
| − | | 6 | 9 | ተቀናሽ |
| = | 5 | 1 | 6 | ልዩነት |

**አሰራር** ፡- ከ 5 ላይ 9 ስለማይችል 10ቤት ከሚገኘዉ 8 ቁጥር ላይ 1 መበደር፡፡ 8 አንድ (1) ሲያበድር 7 ይሆናል፡፡ 5 ደግሞ ከ 8 የተበደረዉን ከፊት 1 ሲያስቀምጥ 15 ይሆናል፡፡ ከዚያም ከ 15 ላይ 9 ሲቀነስ 6 ይሆናል፡፡ በዚህ አይነት ሂደት የማይችል ቁጥር ካለ በመበደር እየቀነሱ መሄድ፡፡

ስለዚህ 583 – 69 = 516

| ለ. | 0 | 12 | 16 | 3 | 18 | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ~~1~~ | ~~3~~ | ~~6~~ | ~~4~~ | ~~8~~ | ዋና |
| − | | 6 | 7 | 2 | 9 | ተቀናሽ |
| = | | 6 | 9 | 1 | 9 | ልዩነት |

ስለዚህ 13,648 - 6,729 = 6,919

| ሐ. | | 6 | 18 | | 2 | 10 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 5 | ~~7~~ | ~~8~~ | 4 | ~~3~~ | ~~0~~ | ዋና |
| − | 2 | 6 | 9 | 1 | 2 | 1 | ተቀናሽ |
| = | 3 | 0 | 9 | 3 | 0 | 9 | ልዩነት |

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

ስለዚህ 578,430 − 269,121 = 309,309 ይሆናል፡፡

| መ. | 3 | 12 | 7 | 12 | 8 | 15 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ~~4~~ | ~~2~~ | ~~8~~ | ~~2~~ | ~~9~~ | ~~5~~ | ዋና |
| − | | 9 | 7 | 3 | 1 | 6 | ተቀናሽ |
| = | 3 | 3 | 0 | 9 | 7 | 9 | ልዩነት |

ስለዚህ 428,295 − 97,316 =330,979

**ምሳሌ** 12:- የአንድ መስሪያ ቤት ሰራተኞች ጠቅላላ የአንድ ወር ደሞዛቸው 789,982 ብር ቢሆንና ግብር መክፈል ለሀገራቸውን ልማትና እድገት ወሳኝ ሚና እንዳለው በመረዳት 160,982 ብር ቢከፍሉ ሰራተኞቹ የሚቀራቸዉ ብር ምን ያህል ነው?

**መፍትሔ** ፡- ጠቅላላ ደሞዝ = 789,982 ብር

ለግብር የሚከፈል = 160,982 ብር

በእጃቸው የሚያገኙት = ጠቅላላ ደሞዝ − ለግብር የሚከፈል ብር

= 789,982 −160,982ብር = 629,000 ብር

ስለዚህ ሰራተኞቹ የሚቀራቸዉ 629,000 ብር ነው፡፡

**አስተዉሉ፡-** መቀነስ የቅይይርም ሆነ የተጣማጅ ባህርይ የለውም::

### መልመጃ 2

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ቀንስ፡፡ ዋናውን፣ ተቀናሹን እና ልዩነቱን ፃፉ፡፡

ሀ. 78,246 −11,111 መ. 971,204 − 342,535

ለ. 771,234 − 342,531 ሠ. 896,543− 672,348

ሐ. 678,803− 569,740

2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ በትክክለኛዉ መልስ ሙሉ፡፡

| ሀ | ለ | ሀ − ለ = መ |
|---|---|---|
| | 100,000 | 400,000 |
| **900,000** | 98,000 | |

## 2.3 መደመርና መቀነስን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች መደመርና መቀነስን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**ተግባር 3**

ጥንድ ጥንድ በመሆን ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ ተወያዩ፡፡ መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

1. በአዲስአበባ ከተማ የኤች አይ ቪ ኤድስ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በ2012 ዓ.ም ግንዛቤ ይወስዳሉ ተብለው ከተለዩት 205,985 ተማሪዎች ውስጥ 10,849 ቢወስዱ፤ ያልወሰዱት ተማሪዎች ስንት ናቸው?

ማስታወሻ

የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ልንከተላቸው የሚገቡ የአሰራር ዘዴዎች፡

- ✓ ጥያቄውን ደጋግመን ማንበብ እና መረዳት
- ✓ የተሰጠውን እና የሚፈለገውን በአግባቡ መለየት
- ✓ በተሰጠው የቃላት ፕሮብሌሞች ውስጥ መጠቀም ያለብንን የሂሳብ ስሌት በትክክል መለየትና ማወቅ
- ✓ ጥያቄውን መስራትና መልሱን ማረጋገጥ

**ምሳሌ 14**፡- በከተማ ግብርና ስራ ዘርፍ ተሰማርተው ህይወታቸውን ለመቀየርና የገቢ ምንጫቸውን ለማሳደግ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ፤ በከብት ማድለብ 36,534፣ በዶሮ እርባታ 28,096፣ በንብ ማነብ 14,010 ቢሆኑ በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ዘርፍ የተሰማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች ስንት ናቸው?

**መፍትሔ ፡-**

$36,534 + 28,096 + 14,010 = 78,640$ በከተማ ግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ናቸው፡፡

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

### መልመጃ 3

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞችን ፍቱ፡፡

1. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ካሉ 3,769 ተማሪዎች መካከል ከትምህርታቸው ጎን ለጎን በፍቃደኝነት በንቃትና በትጋት በተለያዩ ክበቦች ከተሳተፉት 847 በትምህርት ቤቱ በጎ አድራጎት ክበብ፣ 543 ተማሪዎች በነገው ሰው መምህር ክበብ እና 719 ተማሪዎች በአካባቢ እንክብካቤ ክበብ ውስጥ ቢሳተፉ፡-

   ሀ. በሁሉም ክበቦች ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት ተማሪዎች ስንት ናቸው?

   ለ. ምንም ክበብ ውስጥ ያልተሳተፉ ተማሪዎችስ ስንት ናቸው?

2. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት 2,630 ነዉ፡፡ትልቁ ሙሉ ቁጥር 12,347 ነዉ፡፡ ትንሹ ሙሉ ቁጥር ስንት ነዉ?

3. የሁለት ሙሉ ቁጥሮች ልዩነት 15,984 ነዉ፡፡ ትንሹ ሙሉ ቁጥር 480,963 ነዉ፡፡ትልቁ ሙሉ ቁጥር ስንት ነዉ?

4. አንድ ድርጅት እንዴት ውጤታማ የኤሌክትሪክ ፍጆታ አጠቃቀም ተግባራዊ እንደሚያደርግና እንዴት መቀነስ እንደሚችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ወሰደ፡፡ ስልጠና ከመውሰዱ በፊት በአመት 450,984 ብር ቢከፍልና ስልጠና ከወሰደ በኋላ 288,916 ብር ቢከፍል ድርጅቱ በአመት ስንት ብር ቆጠበ?

EDUCATION BUREAU

## የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ

➢ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ

ሀ+ለ = መ ቢሆን ሀ እና ለ ድማሪዎች ይባላሉ፤ መ ደግሞ ድምር ይባላል።

➢ ከማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ ጋር 0 ሲደመር ድምሩ ራሱ ሀ ነው።

ማለትም ሀ+0 = ሀ

➢ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ

ሀ−ለ =መ, ቢሆን ሀ→ዋና፣ ለ →ተቀናሽ፣ መ→ ልዩነት ይባላሉ።

➢ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ

ሀ−ለ = መ ማለት ሀ = ለ+መ እና

ሀ+ለ = መ ማለት ሀ=መ−ለ ፣ ምንግዜም እውነት ናቸው።

➢ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ

- ሀ+ለ = ለ+ሀ, (የመደመር የቅይይር ባህሪ)
- (ሀ+ለ)+መ = ሀ+(ለ+መ), (የመደመር የተጣማጅ ባህሪ)
- ሀ−ለ ≠ ለ−ሀ, (መቀነስ የቅይይርም ባህሪ የለውም)

Government of Addis Ababa
EDUCATION BUREAU

## የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ መልመጃ

1. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ዓ.ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" እና ዓ.ነገሩ ስህተት ከሆነ "ሀሰት" በማለት መልሱ

   ሀ. በማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ላይ 0 ቢደመርበት ድምሩ እራሱ ቁጥሩ ነው፡፡

   ለ. በማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ላይ 0 ሲቀነስ ልዩነቱ 0 ነው፡፡

   ሐ. መቀነስ በሙሉ ቁጥሮች ላይ የቅይይር ባህሪ አለው፡፡

   መ. መደመር በሙሉ ቁጥሮች ላይ የተጣማጅ ባህሪ አለው፡፡፡

2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ድምራቸውን ፈልጉ፡፡

   ሀ. 413+15 ሐ. 3,648+236

   ለ. 978+215,895 መ. 941,809+58,191

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ልዩነታቸውን ፈልጉ

   ሀ. 4,000 - 346 ሐ. 247,365 – 132,151

   ለ. 36,375 – 19,320 መ. 996,370 – 293,478

4. በግብርናው ዘርፍ የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ 200,000 ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለወረዳዎች ለማሰራጨት አቅዶ ከስርጭት የተረፈው 19,897 ኩንታል ቢሆን ለወረዳዎች የተሰራጨት ስንት ኩንታል ማዳበሪያዎች ናቸው?

5. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚገኙ ሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን፣ ሰራተኞችና ተማሪዎች ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ደም ባንክ የደም ልገሳ ለማድረግ ወሰኑ፡፡ በአንደኛው ዙር 1843 በጎ ፈቃደኞች ደም ቢለግሱና በሁለተኛው ዙር 1871 በጎ ፈቃደኞች ቢለግሱ በዚህ መልካም ተግባር ከፍተኛ የደም ልገሳ ያደረጉት በስንተኛው ዙር ነው? በስንት ይበልጣሉ?

6. በአዲስ አበባ ከተማ በምግብ ማቀነባበሪያ ማምረትና ወደ ውጭ በመላክ ለኢትዮጵያ የዶላር ምንዛሬ የሚያስገኝ አንድ ስራ ፈጣሪ ወጣት ያቋቋመው ድርጅት በአንድ ወር 190,000 የአሜሪካን ዶላር የዉጭ ምንዛሬ ለማግኘት ቢያቅድና 180,000 የአሜሪካን ዶላር የወጭ ምንዛሬ ቢያስገኝ ከእቅዱ አንፃር ያልተሳካው ስንት የአሜሪካን ዶላር ነው?

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

# ምዕራፍ 3 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል

**የመማር ማስተማር ውጤቶች፡-ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-**

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት ትችላለችሁ፡፡
- ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትፈታላችሁ፡፡
- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል ትችላላችሁ፡፡
- ማካፈልን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን ትፈታላችሁ፡፡

**መግቢያ**

በሶስተኛ ክፍል የሂሳብ ትምህርታችሁ እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እና ማካፈል ትማራላችሁ፡፡

## 3.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት

### 3.1.1 የ10,000፣ የ100,000 እና በላይ ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

3.1.1.1 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**ተግባር 1**

በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ

1. ብዜታቸውን ፈልጉ

   ሀ. $20 \times 4$ ለ. $100 \times 3$ ሐ. $450 \times 2$ መ. $83 \times 8$

2. አንድ ተማሪ ከትምህርት ሰዓት ውጭ ያለውን ትርፍ ጊዜ ለደብተርና ለአንዳንድ የትምህርት ቁሳቁስ ማሟያ በመኖሪያ ቤቱ 3 እንቁላል ጣይ ዶሮዎችን በማርባት በአንድ ሳምንት 18 እንቁላሎችን ለገበያ ቢያቀርብ በ9 ሳምንታት ወስጥ ስንት እንቁላል ለገበያ ያቀርባል?

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

3. ከዚህ በታች ከቀረበው ብዜት ሰንጠረዥ ምን ተረዳችሁ?

| × | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 2 | 2 | 4 | 6 | 8 | 10 | 12 | 14 | 16 | 18 | 20 | 22 | 24 |
| 3 | 3 | 6 | 9 | 12 | 15 | 18 | 21 | 24 | 27 | 30 | 33 | 36 |
| 4 | 4 | 8 | 12 | 16 | 20 | 24 | 28 | 32 | 36 | 40 | 44 | 48 |
| 5 | 5 | 10 | 15 | 20 | 25 | 30 | 35 | 40 | 45 | 50 | 55 | 60 |
| 6 | 6 | 12 | 18 | 24 | 30 | 36 | 42 | 48 | 54 | 60 | 66 | 72 |
| 7 | 7 | 14 | 21 | 28 | 35 | 42 | 49 | 56 | 63 | 70 | 77 | 84 |
| 8 | 8 | 16 | 24 | 32 | 40 | 48 | 56 | 64 | 72 | 80 | 88 | 96 |
| 9 | 9 | 18 | 27 | 36 | 45 | 54 | 63 | 72 | 81 | 90 | 99 | 108 |
| 10 | 10 | 20 | 30 | 40 | 50 | 60 | 70 | 80 | 90 | 100 | 110 | 120 |
| 11 | 11 | 22 | 33 | 44 | 55 | 66 | 77 | 88 | 99 | 110 | 121 | 132 |
| 12 | 12 | 24 | 36 | 48 | 60 | 72 | 84 | 96 | 108 | 120 | 132 | 144 |

## ማስታወሻ

- ሙሉ ቁጥሮችን ለማባዛት ሁልጊዜ ከአንድ ቤት መጀመር ወደ ግራ እያባዛን እንሄዳለን፡፡

**ምሳሌ 1፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ

ሀ. $30 \times 4$ ለ. $100 \times 5$ ሐ. $298 \times 3$ መ. $480 \times 2$ ሠ. $93 \times 9$

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 30
$\underline{\times 4}$
$= 120$

ለ. 100
$\times \underline{\ \ 5}$
$= 500$

ሐ. 298
$\underline{\times 3}$
$= 894$

መ. 480
$\underline{\times \ \ 2}$
$= 960$

ሠ. 93
$\times 9$
$= 837$

**ምሳሌ 2፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቤት ዋጋቸው በመተንተን ግለጹ

ሀ. 468 ለ. 975

**መፍትሔ፡-**

ሀ. $468 = 400 + 60 + 8$
$= 4 \times 100 + 6 \times 10 + 8 \times 1$

ለ. $975 = 900 + 70 + 5$
$= 9 \times 100 + 7 \times 10 + 5 \times 1$

**ምሳሌ 3፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመተንተን አባዙ፡፡

ሀ. 34 × 4 ለ. 102 ×5 ሐ. 64 × 3 መ. 48 ×2

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 34 ማለት 30+4 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል 34 × 4 የሚለው (30+4) ×4

= (30 × 4) + (4× 4) = 120+16 = 136

ስለዚህ 34 × 4= 136

ለ. 102 ማለት 100+2 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል 102 × 5 የሚለው

(100+2) ×5= (100 × 5) + (2× 5) = 500+10= 510

ስለዚህ 102 × 5= 510

ሐ. 64 ማለት 60+4 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል 64 × 3 የሚለው

(60+4) ×3= (60 × 3) + (4× 3) = 180+12= 192

ስለዚህ 64 × 3= 192

መ. 48 ማለት 40+8 ማለት ነው፡፡ በመቀጠል 48 ×2 የሚለው

(40+8) ×2= (40 × 2) + (8× 2) = 80+16 = 96

ስለዚህ 48 × 2=96

## መልመጃ 1

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

   ሀ. 50 × 2 ለ. 300 ×3 ሐ. 208 × 4 መ. 89 ×5 ሠ. 98 × 7

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በቤት ዋጋቸው በመተንተን ጻፉ፡፡

   ሀ. 684 ለ. 789 ሐ. 843 መ. 980

3. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመተንተን አባዙ፡፡

   ሀ. 54 × 2 ለ. 302 ×3 ሐ. 82 × 4 መ. 98 ×5 ሠ. 175 × 6

4. በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ጤናማ እና አምራች ትውልድን ለመፍጠር የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ጠቃሚ መሆኑን ከተገነዘቡ በኋላ ባላቸው ቦታ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን እያመረቱ ይመገባሉ፡፡ የተረፋቸውን ወደ ገበያ በመውሰድ በአንድ ሳምንት 129 ብር ቢሸጡ፤ በ7 ሳምንት ምን ያህል ብር ይሸጣሉ?

EDUCATION BUREAU

### 3.1.1.2 እስከ 1,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማባዛት

**ተግባር 2፡-**

ጥንድ ጥንድ በመሆን ጥያቄዎችን ስሩ፡፡ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

   ሀ. $9 \times 10$ ለ. $10 \times 10$ ሐ. $50 \times 0$ መ. $80 \times 10$

2. በአንድ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች በሒሳብ ትምህርታቸው ውጤታማ ለመሆን በሳምንት ለ5 ሰዓቶች የማጠናከሪያ ትምህርት ቢማሩ በ10 ሳምንት ውስጥ ስንት ሰዓቶች ይማራሉ?

**ማስታወሻ፡-**

- ማንኛውም ከዜሮ የተለየ ሙሉ ቁጥር በ10 ለማባዛት ሙሉ ቁጥሩን ፅፈን ከቁጥሩ በስተቀኝ በኩል 0 መጨመር ነው፡፡
- ሁል ጊዜ ስናባዛ ከአንድ ቤት ዋጋ መጀመር አለብን፡፡

**ምሳሌ 4**፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በ10 አባዙ፡፡

ሀ. $30 \times 10$ ለ. $100 \times 10$ ሐ. $298 \times 10$ መ. $480 \times 10$

**መፍትሔ፡-** ሙሉ ቁጥር በ10 ለማባዛት ሙሉ ቁጥሩን ፅፈን ከቁጥሩ በስተቀኝ በኩል 0 መጨመር ነው፡፡

ሀ $30 \times 10 = 300$ ለ $100 \times 10 = 1{,}000$

ሐ $298 \times 10 = 2{,}980$ መ $480 \times 10 = 4{,}800$

**ምሳሌ 5፡-**

በአንድ ትምህርት ቤት የምትማር አንዲት ተማሪ ከትምህርት ሰዓት ውጭ ያላትን ትርፍ ጊዜዋን ወላጆቿን በማገዝና ውጤታማ ጥናት በማጥናት ታሳልፋለች፡፡ ተማሪዋ በአንድ ወር ውስጥ ለ120 ሰዓት ብታጠና በ10 ወር ውስጥ ምን ያህል ሰዓት ታጠናለች?

**መፍትሔ** ፡-

በ1 ወር = 120 ሰዓታት

በ10 ወራት= ?

ስለዚህ $120 \times 10 = 1{,}200$ ሰዓታት ታጠናለች፡፡

Addis Ababa ... Education Bureau

### መልመጃ 2

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በ10 አባዙ፡፡

   ሀ. 64 ለ. 302 ሠ. 775

   ሐ. 982 መ. 598

2. አንድ ድርጅት ውጤታማ የኤሌክትሪክ ፍጆታ አጠቃቀም ተግባራዊ ለማድረግ የአጠቃቀም ስልጠና ወሰደ፡፡ በስልጠናው በአንድ ዓመት 658 ብር ቢከፍል በ10 አመት ስንት ብር ይከፍላል?

## 3.1.2 ሙሉ ቁጥሮችን የማባዛት ስልቶች

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

❖ የማባዛት ስልቶችን መረዳት፡፡

**ተግባር 3፡-**

የሚከተለውን ጥያቄ በቡድን በመሆን ተወያዩ፡፡

1. ሙሉ ቁጥሮችን ለማባዛት የምንከተላቸውን ዘዴዎች ዘርዝሩ፡፡

**ሙሉ ቁጥሮችን የማባዛት ስልቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡**

### 3.1.2.1 በአእምሮአችን ከፋፍለን የማባዛት ስልት

ይህ የማባዛት ስልት ቁጥሮችን በ10 ብዜትና በባለ 1 ሆሄ በመከፋፈል የማባዛት ስልት ነው፡፡

**ምሳሌ 6** 43 × 6 በቀላሉ ለማባዛት (40+3)×6 በማድረግ መጠቀም ሲሆን ይህም

**43 × 6 =**

40 + 3

× 6 ⇩

240 + 18 = **258**

### 3.1.2.2 ግሪድ የማባዛት ዘዴ ( በሰንጠረዥ የማባዛት ዘዴ)

ይህ የማባዛት ዘዴ ከላይ ያየነውን የማባዛት ስልት የመመዝገብ ዘዴ ሲሆን በሰንጠረዥ በመስራት በመደመር (በመቀነስ) ብዜትን የማግኘት ስልት ነው፡፡

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 7**፡- 68×6 የሚለውን በቀላሉ ለማግኘት **በመደመር** መስራት

| × | 6 |
|---|---|
| 60 | 360 |
| 8 | +48 |
| በድምር ብዜት | =408 |

**ይህ ማለት** $60 \times 6 + 8 \times 6 = 360 + 48 = 300 + 60 + 40 + 8 = 300 + 100 + 8 = 400 + 8 = 408.$

በሌላ መልኩ 68×6 የሚለውን በቀላሉ ለማግኘት **በተመሳሳይ በመቀነስ መስራት**

| × | 6 |
|---|---|
| 70 | 420 |
| 2 | −12 |
| በልዩነት ብዜት | =408 |

**ይህ ማለት** $68 \times 6 = (70 - 2) \times 6 = (70 \times 6) - (2 \times 6) = 420 - 12 = 408$

**ምሳሌ 8**፡- 152×13 የሚለውን በቀላሉ ለማግኘት በመደመር

152 $= 100 + 50 + 2$ እና 13$= 10 + 3$

| × | 100 | 50 | 2 |
|---|---|---|---|
| 10 | 1,000 | 500 | 20 |
| 3 | 300 | 150 | 6 |
| በድምር ብዜት | =1,300 | 650 | 26 |

**በድምሩ** $1,300 + 650 + 26 = 1,300 + 600 + 50 + 20 + 6$

$= 1,976$ ብዜት

EDUCATION BUREAU

### 3.1.2.3 በመስመር የማባዛት ስልት

ይህ የማባዛት ስልት የሚባዙ ቁጥሮችን ከውጭ በመፃፍ በቀጥታ በማባዛት በዲያጎናል መስመር በመደመር ይገኛል፡፡

**ምሳሌ 9** የሚከተሉትን አባዙ

ሀ. 457×6 ለ. 235×4 ሐ. 169,036×5

**መፍትሔ ሀ**




ስለዚህ 457× 6 = 2,742




ስለዚህ 235 × 4 = 940




ስለዚህ 169,036 × 5 = 845,180

## በረጅሙ ቁልቁል የማባዛት ስልት

ሙሉ ቁጥሮችን በቤት ዋጋቸው በመፃፍ በቁሉቁል ማባዛት ፡፡

**ምሳሌ 10፡-** 274×4 = 2 7 4
× 4
=1,096

**መልመጃ 3**

1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች የተለያዩ የማባዛት ስልቶችን በመጠቀም ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

ሀ.700 × 10 ሐ.436 × 5 ረ. 8,152 × 7

ለ.741 × 9 መ.1245 × 3 ሠ. 972 × 8

**የተግባር ስራ፡-**

የተለያዩ የማባዛት ስልቶችን የሚያሳይ ስዕል ወይም ሞዴል ሰርታችሁ እንዴት ማባዛትን በቀላሉ ማወቅና መረዳት እንዳለባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማብራራት ግለፁ።

### 3.1.3 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

### 3.1.5.3 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ማባዛት

**ተግባር 4፡-**

በቡድን በመሆን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከሰራችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሏቸዉ።

1. እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን ዘርዝሩ።
2. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ1,000 ብዜት የሆኑትን ሙሉ ቁጥር በ8 አባዙ።

   ሀ. 2,500 ለ. 840 ሐ. 9,000 መ. 690 ረ. 5,000

**ማስታወሻ፡-**

❖ ማንኛውም የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ሀ ን በባለ አንድ ሆሄ ስናበዛ ዜሮ ያልሆኑትን በጥንቃቄ ካባዛን በኋላ ሶስት ዜሮ መጨመር ይኖርብናል።

**ምሳሌ 11**፡-የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ።

ሀ. $3,000\times 4$ ለ. $8,000\times 7$ ሐ. $4,000\times 2$ መ. $9,000\times 9$

**መፍትሔ፡-**

ሀ. በመጀመሪያ $3\times 4 = 12$፣ በመቀጠል 12 ላይ በቀኝ በኩል ሶስት ዜሮ እንጨምራለን። ስንጨምርም 12,000 ይሆናል።

ስለዚህ $3,000\times 4 = 12,000$.

ለ. በመጀመሪያ $8\times 7 = 56$፣ በመቀጠል 56 ላይ በቀኝ በኩል ሶስት ዜሮ



[stamp] ... of Addis Ababa ... EDUCATION BUREAU

እንጨምራለን። ስንጨምርም 56,000 ይሆናል።

ስለዚህ $8{,}000 \times 7 = 56{,}000$ .

ሐ. በመጀመሪያ $4 \times 2 = 8$፣ በመቀጠል8 ላይ በቀኝ በኩል ሶስት ዜሮ

እንጨምራለን። ስንጨምርም 8,000 ይሆናል። ስለዚህ $4{,}000 \times 2 = 8{,}000$

መ. በመጀመሪያ $9 \times 9 = 81$፣ በመቀጠል 81 ላይ በቀኝ በኩል ሶስት ዜሮ

እንጨምራለን። ስንጨምርም 81,000 ይሆናል።

ስለዚህ $9{,}000 \times 9 = 81{,}000$

**መልመጃ 4**

1. የሚከተሉትን ቁጥሮች ብዜታቸዉን ፈልጉ።

   ሀ. $9{,}000 \times 5$ ሐ. $3{,}000 \times 7$ ሠ. $2{,}000 \times 0$

   ለ. $5{,}000 \times 1$ መ. $8{,}000 \times 4$

2. በ2,500 እና በ8,000 መካከል ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በመዘርዘር በ5 አባዙ።

### 3.5.1.3 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በ10 ማባዛት

**ተግባር 5፡-**

በቡድን በመሆን ጥያቄዎችን ስሩ።

1. ከሚከተሉት ዉስጥ የ1000 ብዜት የሆኑትን ከለያችሁ በኋላ በ10 አባዙ።

   ሀ 2,000 ለ 6,000 ሐ 6,890 መ 999 ረ 7,000

**ማስታወሻ፡-**

❖ አንድ ሙሉ ቁጥር የ1,000 ብዜት ነው የምንለው ከቁጥሩ በቀኝ በኩል ቢያንስ ሶስት ዜሮ ሲኖሩት ነው።

**ምሳሌ12፡-**

1. ከ3,000 እስከ 7,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን ዘርዝሩ።
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ።

   ሀ. $4{,}000 \times 10$ ለ. $8{,}000 \times 10$ ሐ. $10{,}000 \times 10$

**መፍትሔ ፡-**

1. ከ3,000 እስከ 7,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡
   4,000፣ 5,000 እና 6,000
2. ሀ. $4000 \times 10 = 40{,}000$ ምክንያቱም 4000 ላይ በቀኝ በኩል አንድ ዜሮ መጨመር
   ለ. $8{,}000 \times 10 = 80{,}000$ ምክንያቱም 8,000 ላይ በቀኝ በኩል አንድ ዜሮ መጨመር
   ሐ. $10{,}000 \times 10 = 100{,}000$ ምክንያቱም 10,000 ላይ በቀኝ በኩል 1 ዜሮ መጨመር

**መልመጃ 5**

1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ1000 ብዜቶች የሆኑትን በ10 አባዙ፡፡
   ሀ. 2,000 ለ. 8,100 ሐ. 3,200 መ. 1,000 ረ. 9,000
2. በ4,500 እና በ10,000 መካከል ያሉ የ1,000 ብዜቶችን ዘርዝሩ፡፡

### 3.1.4 እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

❖ እስከ 100,000 ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**ተግባር 6፡-**

በቡድን በመሆን ጥያቄዎችን ስሩ፡፡

1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ10,000 ብዜቶችን ለይታችሁ በ4 አባዙ፡፡
   ሀ. 10,000 ለ. 20,500 ረ.90,000
   ሐ. 70,000 መ. 34,000

**ማስታወሻ፡-**

❖ ማንኛውም የ10,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ሀ ን በባለ አንድ ሆሄ ስናበዛ ዜሮ ያልሆኑትን በጥንቃቄ ካባዛን በኋላ በቀኝ በኩል መጨረሻ ላይ አራት ዜሮ መጨመር ነው፡፡

❖ የ10,000 ብዜት የሆነ ሙሉ ቁጥር ሁሉ የ1,000 ብዜት ይሆናል፡፡

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ13፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

ሀ. 30,000 × 10 ለ. 20,000× 5 ሐ. 90,000× 10

**መፍትሔ፡-**

ሀ. በመጀመሪያ 3× 1 = 3፣ በመቀጠል 3 ላይ በቀኝ በኩል መጨረሻ ላይ አራት ዜሮ እንጨምራለን፡፡ ይህም **300,000 ይሆናል፡፡**

**ስለዚህ** $30{,}000 \times 10 = 300{,}000.$

በተመሳሳይ አሰራር

ለ. 20,000× 5 =100,000

ሐ. 90,000× 10 = 900,000

መልመጃ 6

1. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች መካከል የ10,000 ብዜቶች የሆኑትን በመለየት በ6 አባዙ፡፡

ሀ. 10,000 ለ. 30,000 ሐ. 9,800 መ. 70,000 ረ. 15,900

2. በ29,000 እና በ51,000 መካከል ያሉ የ10,000 ብዜቶችን በመዘርዘር በ8 አባዙ፡፡

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

ሀ. 60,000× 3 ሐ. 70,000 × 4

ለ. 20,000 × 5 መ. 100,000 × 9

### 3.1.5 ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

**የንዑስ ርእስ የመማር ብቃት፡-**

- ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማባዛት

### 3.1.5.1 ብዜታቸው እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ ቁጥር ማባዛት

**ተግባር 7፦**

ሁለት ሁለት በመሆን የሚከተለውን ጥያቄ ተወያዩበት።

1. የአንድ የእርዳታ ድርጅት የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማንን ለመደገፍ 10,000 ኪሎ ግራም የጤፍ ዱቄት በ1ኛ ዙር ለገሰ። በ9 ዙሮች ስንት ኪሎ ግራም የጤፍ ዱኬት ይለግሳሉ?

**ማስታወሻ**

ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ ፡

ሀ×ለ=መ ቢሆን **ሀ → ተባዥ ፣ ለ→ አብዥ፣ መ→ ውጤት (ብዜት) ይባላል።**

➢ ሙሉ ቁጥሮችን ማባዛት እኩል ተደማሪዎች የመደመር አጭር መንገድ ነው።

## አለኝታ የሌላቸዉን ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

**ምሳሌ 14** ፦የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ።

ሀ. 324 × 2 ለ. 211 × 7 ሐ. 501 × 4 መ. 9,023 × 3

**መፍትሔ** ፦ሰንጠረዥ በመጠቀም ማባዛት

ሀ. 324 × 2

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አለኝ | | | | |
| | 3 | 2 | 4 | ተባዥ |
| × | 2 | | | አባዥ |
| = | 6 | 4 | 8 | ብዜት |

ስለዚህ 324 × 2=648 ይሆናል።

ለ. 211 × 7

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አለኝ | | | | |
| | 2 | 1 | 1 | ተባዥ |
| × | 7 | | | አባዥ |
| = | 14 | 7 | 7 | ብዜት |

ስለዚህ211 × 7= 1,477 ይሆናል።

ሐ 501 × 4

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አለኝ | | | | |
| | 5 | 0 | 1 | ተባዥ |
| × | 4 | | | አባዥ |
| = | 20 | 0 | 4 | ብዜት |

ስለዚህ 501× 4 = 2,004

መ 9,023 × 3

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አለኝ | | | | | |
| | 9 | 0 | 2 | 3 | ተባዥ |
| × | 3 | | | | አባዥ |
| = | 27 | 0 | 6 | 9 | ብዜት |

ስለዚህ 9023× 3 = 27,069

## አለኝታ ያላቸዉን ሙሉ ቁጥሮች ማባዛት

**ምሳሌ 15**፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ፡፡

ሀ. 97,304 × 5 ለ. 84,613 × 6 ሐ. 100,163 ×9 መ. 413,265 × 2

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 97,304 × 5

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አለኝ | +3 | +1 | | +2 | | |
| | 9 | 7 | 3 | 0 | 4 | ተባዥ |
| × | 5 | | | | | አባዥ |
| = | 48 | 6 | 5 | 2 | 0 | ብዜት |

ስለዚህ 97,304 × 5 = 486,520 ይሆናል፡፡

ለ. 84,613 × 6

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አለኝ | +2 | +3 | | +1 | | |
| | 8 | 4 | 6 | 1 | 3 | ተባዥ |
| × | 6 | | | | | አባዥ |
| = | 50 | 7 | 6 | 7 | 8 | ብዜት |

ስለዚህ84,613 × 6 =507,678 ይሆናል፡፡

ሐ.100,163 ×9

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አለኝ** | | | +1 | +5 | +2 | | |
| | 1 | 0 | 0 | 1 | 6 | 3 | ተባዥ |
| × | 9 | | | | | | አባዥ |
| = | 9 | 0 | 1 | 4 | 6 | 7 | ብዜት |

ስለዚህ 100,163 ×9 =901,467 ይሆናል።

መ. 413,265 × 2

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **አለኝ** | | | | +1 | +1 | | |
| | 4 | 1 | 3 | 2 | 6 | 5 | ተባዥ |
| × | 2 | | | | | | አባዥ |
| = | 8 | 2 | 6 | 5 | 3 | 0 | ብዜት |

ስለዚህ413,265 × 2 = 826,530 ይሆናል።

**ምሳሌ 16**፦ የአንድ ቤተሰብ የአንድ ወር የቤት ወጭ 15,798 ብር ቢሆን ቤተሰቡ በ9 ወራት ውስጥ ስንት ብር ወጪ ያደረጋል?

**መፍትሔ፦**

የ1 ወር ወጪ= 15,798 ብር

የ9 ወራት ወጪ =15,798 ብር× 9= 142,182 ብር

ስለዚህ በ9 ወራት ውስጥ የቤተሰቡ ጠቅላላ ወጭ 142,182 ብር ይሆናል።

## መልመጃ 7

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ

| ሀ. | ለ. | ሐ. | መ. | ሠ. | ረ. |
|---|---|---|---|---|---|
| 143 | 3,619 | 14,008 | 42,239 | 100,001 | 470,450 |
| × 5 | × 6 | × 7 | × 8 | × 9 | × 2 |

2. የሚከተሉትን ቁጥሮች ብዜታቸውን ">", "<" ወይም "=" በመጠቀም አወዳድሩ፡፡

ሀ. 68 × 8 ______ 8 × 64　　　　መ. 304,005 × 3 ____ 279,098 × 2

ለ. 708 × 3 ______ 602 × 4　　　　ሠ. 450,000 × 2 ______ 300,000 × 3

ሐ. 9,312 × 8 ______ 10,306 × 9

## የማባዛት የቅይይር እና የተዛማጅ ባህሪ

**ተግባር 8፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን በመፈለግ አወዳድሩ እና የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

ሀ. 88 × 22 እና 22 × 88　　　　ሐ. (3 × 4) × 6 እና 3 × (4 × 6)

ለ. 94 × 10 እና 10 × 94　　　　መ. (12 × 7) × 9 እና 12 × (7 × 9)

**ማስታወሻ**

ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ ፣ለ እና መ

✓ ሀ×ለ = ለ×ሀ የማባዛት የቅይይር ባህሪ ተብሎ ይጠራል፡፡

✓ (ሀ×ለ)× መ = ሀ×(ለ×መ) የማባዛት የተጣማጅ ባህሪ ይባላል፡፡

City Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 17**፡-የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን በመፈለግ አወዳድሩ

ሀ. $16 \times 8$ እና $8 \times 16$ ሐ. $(6 \times 10) \times 32 = 6 \times (10 \times 32)$

ለ. $710 \times 9$ እና $9 \times 710$

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 16

$\underline{\times 8}$

$=\underline{\mathbf{128}}$

ስለዚህ $16 \times 8 = 128 = 8 \times 16$( የማባዛት የቅይይር ባህሪ)

ለ. 710

$\underline{\times 9}$

$= 6{,}390$

ስለዚህ $710 \times 9 = 6{,}390 = 9 \times 710$ (የማባዛት የቅይይር ባህሪ)

ሐ. $(6 \times 10) \times 32 = 6 \times (10 \times 32)$

$(6 \times 10) \times 32$, በመጀመሪያ ቅንፍ ይሬራል፡፡

10

$\underline{\times 6}$

$= 60$

በመቀጠል $60 \times 32 = 32$

$\underline{\times 60}$

$= 1{,}920$

ስለዚህ $(6 \times 10) \times 32 = 60 \times 32 = 1{,}920 = 6 \times (10 \times 32)$

( የማባዛት የተጣማጅ ባህሪ )

### መልመጃ 8

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ብዜታቸውን ፈልጉ፡፡

   ሀ. $16 \times (8 \times 10)$ ሐ. $(9 \times 40) \times 8$

   ለ. $10 \times (9 \times 80)$ መ. $(6 \times 10) \times 20$

2. በባዶ ቦታውን ላይ ትክክለኛውን መልስ በማስገባት መልሱ፡፡

   ሀ. $18 \times 6 =$ ______ $\times 18$

   ለ. $230 \times 20 = 20 \times$ ______

   ሐ. $(20 \times 14) \times 15 =$ ______ $\times (14 \times 15)$

   መ. (______ $\times 50) \times 9 = 34 \times (50 \times$ ____ $)$

### 3.1.5.2 ብዜታቸው ከ1,000,000 የሚያንሱ ሙሉ ቁጥሮችን በ10 ማባዛት

**ማስታወሻ**

- ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር በ10 ለማባዛት ተባዥውን ቁጥር በመውሰድ ከተባዥ ቁጥሩ በስተቀኝ መጨረሻ ላይ ዜሮ መጨመር፡፡
- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በዜሮ ሲባዛ ውጤቱ ዜሮ ነው፡፡

**ምሳሌ 18**፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ ፡፡

ሀ. $1100 \times 10$ ለ. $1220 \times 10$ ሐ. $4900 \times 10$ መ. $10,000 \times 10$

ሠ. $37,650 \times 10$ ረ. $100,000 \times 10$ ሰ. $99,982 \times 10$

**መፍትሔ**፡-

ሀ. $1100 \times 10 = 11,000$

ለ. $1220 \times 10 = 12,200$

ሐ. $4900 \times 10 = 49,000$

መ. $10,000 \times 10 = 100,000$

ረ. $100,000 \times 10 = 1,000,000$

ሠ. $37,650 \times 10 = 376,500$

ሰ. $99,982 \times 10 = 999,820$



✓ (ሀ×ለ)× መ = ሀ×(ለ×መ) የማባዛት የተጣማጅ ባህሪ ይባላል፡

## መልመጃ 9

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን ፈልጉ።

ሀ. 9,635 $\times 10$    ሐ. 24,390 $\times 10$    ሠ. 75,413 $\times 10$

ለ. 100,000 $\times 10$    መ. 90,000 $\times 10$    ረ. 12,300 $\times 10$

2. በባዶ ቦታውን ትክክለኛውን አሀዝ በማስገባት መልሱ።

ሀ. ______ $\times 10 = 6{,}870$    ሐ. ____ $\times 87{,}964 = 879{,}640$

ለ. 3,600$\times$ 10 =________    መ. (______ $\times$ 80) $\times$ 90 =10$\times$ (80 $\times$ ____ )

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

### 3.1.6 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 2 እና በላይ ሆሄያቶች ማባዛት

**ተግባር 9**

የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች ብዜታቸውን በመፈልግ የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

ሀ. $880 \times 122$ ሐ. $458 \times 160$

ለ. $940 \times 80$ መ .$4,500 \times 90$

**ምሳሌ** 19፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ።

ሀ. 67,314 × 12 ለ. 4,685 × 172

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 67,314
× 12
134,628
+67,314
= **807,768**

ለ. 4,685
× 172
9,370
32,795
+4,685
=**805,820**

መልመጃ 10

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አባዙ

ሀ. 14,123 × 215 ለ. 3,619 × 46 ሐ. 14,008 × 87 መ. 42,239 × 28

**2.** በአንድ ክልል ውስጥ 48,597 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች መፈተኛ ክፍል ቢኖርና በአንድ ክፍል ከሚፈተኑት ተማሪዎች 36ቱ ሴቶች ቢሆኑ በጠቅላላው ስንት ሴት ተማሪዎች ይፈተናሉ?

Addis Ababa ... Curriculum Bureau

### 3.1.7 ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- ማባዛትን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**ተግባር** 10

ጥንድ ጥንድ በመሆን ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ፡፡

1. በአንድ መስሪያ ቤት 10 ኮምፒዉተሮች አሉ፡፡ የአንዱ ኮምፒዉተር ዋጋ 19,000 ብር ቢሆን የአጠቃላይ ኮምፒዉተሮች ዋጋ ምን ያህል ነው?

**ማስታወሻ**

- የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ልንከተላቸው የሚገቡ የአሰራር ዘዴዎች፡
  - ✓ ጥያቄውን ደጋግመን ማንበብ እና መረዳት
  - ✓ የተሰጠውን እና የሚፈለገውን በአግባቡ መለየት
  - ✓ በተሰጠው የቃላት ፕሮብሌሞችን ውስጥ መጠቀም ያለብንን የሂሳብ ስሌት በትክክል መለየትና ማወቅ
  - ✓ ጥያቄውን መስራትና መልሱን ማረጋገጥ

**ምሳሌ** 21፡- በቱሪዝም ዘርፍ በ2011 ዓ.ም ሀገራችን ኢትዮጵያ ያላትን የተፈጥሮ መስዕብ ለመጎብኘት ከሚመጡ የውጭና የውስጥ ጎብኚዎች በወር 97,840 ገቢ ብር ቢገኝ በዘጠኝ ወራት ሀገራችን ኢትዮጵያ ከጎብኞች ስንት ብር ታገኛለች?

**መፍትሔ፡-**

$97,840 \times 9 = 880,560$

ስለዚህ ሀገራችን ኢትዮጵያ በ 9 ወራት 880,560 ብር ታገኛለች፡፡

**መልመጃ 11**

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞችን ፍቱ፡፡

1. በአንድ አካባቢ የወንዝ ዳርቻዎችን ንፁህ ለማድረግ የተለያዩ ፕላስቲኮችን ሰብስቦ ለፋብሪካ በማቅረብ የስራ እድል ፈጠራ የተደራጁ 4,609 ወጣቶች እያንዳንዳቸው 8 ኪ.ግ ፕላስቲኮችን እየሰበሰቡ ገቢ ቢያገኙ በአጠቃላይ ምን ያህል ኪ.ግ ፕላስቲክ ለፋብሪካው ያቀርባሉ?
2. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 2,500 ተማሪዎች አሉ፡፡ እያንዳንዳቸው 9 የመማሪያ መፅሃፍት ቢወስዱ በአጠቃላይ ምን ያህል መፅሃፍት ወሰዱ?
3. በኢትዮጵያ ዜጎችን በመርዳት ላይ አተኩረው የሚሰሩ 35 ባለሀብቶች የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለሚጠብቁ፣ ህይወታቸውን ለሀገር እየሰጡ ላሉ ለኢትዮጵያ ሀገር መከላከያ ሰራዊት እያንዳንዳቸው 200,000 ብር ማበረታቻ ቢሰጡ በጠቅላላው ባለሀብቶቹ ስንት ብር ሰጡ?

## 3.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን ማካፈል

### 3.2.1 እስከ 1,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማካፈል

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እስከ 1,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማካፈል

#### 3.2.1.1 እስከ 1,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን በባለ1 ሆሄ ማካፈል

**ተግባር 1፡-**

1. የ100 ብዜት ከሆኑት ቁጥሮች ውስጥ ቢያንስ 5 ምሳሌ ስጡ፡፡
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ $200 \div 2$ ለ $300 \div 6$ ሐ $600 \div 5$ መ $900 \div 3$

**ማስታወሻ**

- የአንድ ቤታቸውና የአስር ቤታቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች የ100 ብዜቶች ይባላሉ፡፡

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**ምሳሌ 1**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 200÷ 5 ለ. 300 ÷ 3 ሐ. 800 ÷ 5 መ. 900 ÷ 9

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 200÷ 5 = (20× 10) ÷ 5
= 20×(10 ÷5)
= 20× 2
= 40

ለ. 300 ÷ 3 = (30× 10) ÷ 3
= 10× (30 ÷3)
= 10× 10
= 100

ሐ. 800÷ 5 = (80× 10) ÷ 5
= 80×(10 ÷5)
= 80×2
= 160

መ. 900 ÷ 9 = (90× 10) ÷ 9
= 10×(90 ÷9)
= 10×10
= 100

**መልመጃ 1**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 300 ÷ 2 ሐ. 400 ÷ 5 ሠ. 900 ÷ 6

ለ. 600 ÷ 3 መ. 700 ÷ 5 ረ. 800 ÷ 8

2. አንድ የህብረት ስራ ማህበር 1,000 ኩንታል ስኳር ለ8 ነጋዴዎች እኩል ቢያከፋፍል ለእያንዳንዱ ነጋዴ ስንት ኩንታል ስኳር ይደርሳቸዋል?

### 3.2.1.2 እስከ 1,000 ያሉ የ100 ብዜቶችን በ10 ማካፈል

**ተግባር 2፡-**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ 100÷10 ለ 300÷10 ሐ 700÷10 መ 800÷10

2. አንድ መምህር ለ10 የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች 100 ደብተሮችን እኩል ቢያከፋፍሉ፤ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስንት ደብተር ይደርሳቸዋል?

Government ... EDUCATION

## ማስታወሻ

- የመቶ ብዜት የሆነን ቁጥር ለ10 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤትሆሄ 0 በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው፡፡
- በማካፈል የሚገኘው ውጤት በማባዛት ይረጋገጣል፡፡
- ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለ1 ሲካፈል ዉጤቱ እራሱ ቁጥሩ ነው፡፡

**ምሳሌ 2፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 900 ÷ 10 ለ. 700÷10 ሐ. 1000 ÷10

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 900÷ 10 =90 ምክንያቱም የመቶ ብዜትን በ10 በምናካፍልበት ጊዜ የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኝ ቁጥር ስለሆነ

**ማረጋገጫ** 10×90=900

ለ. 700÷ 10 = 70 ምክንያቱም የመቶ ብዜትን በ10 በምናካፍልበት ጊዜ የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኝ ቁጥር ስለሆነ

ማረጋገጫ፡10×70=700

ሐ. 1000÷ 10 =100 ምክንያቱም የመቶ ብዜትን በ10 በምናካፍልበት ጊዜ የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኝ ቁጥር ስለሆነ

**ማረጋገጫ** 10×100=1000

### መልመጃ 2

1. በ100 እና በ1,000 መካከል የሚገኙ የ100 ብዜቶችን ዘርዝሩ፡፡
2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

   ሀ. 100 ÷ 10 ለ. 300 ÷10 ሐ. 600 ÷10 መ. 500 ÷ 10
3. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ 400 የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች አሉ፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በ10 እኩል ክፍሎች ቢመደቡ በአንድ ክፍል ወስጥ ስንት ተማሪዎች ይመደባሉ?

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## 3.2.2 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማካፈል

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- እስከ10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1ሆሄ እና በ10 ማካፈል

### 3.2.2.1 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ማካፈል

**ተግባር 3 ፡-**

1. ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩባቸው፡፡

ሀ. 1000 ÷ 4 ለ. 5000 ÷ 2 ሐ. 6000 ÷5 መ. 9000 ÷ 3

**ማስታወሻ**

- የ1,000 ብዜቶች የምንላቸው የአንድ ቤት፣ የአስር ቤት እና የመቶ ቤታቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው፡፡

**ምሳሌ 3፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 1,000 ÷ 2 ለ. 2,000 ÷ 5

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 1,000÷ 2 =(100× 10) ÷ 2
= 100×(10÷2)
= 100×5
= 500

ለ. 2,000÷ 5 = (20× 100) ÷ 5
= 100×(20÷5)
= 100×4
= 400

**ምሳሌ 4፡-** ትልቁን ባለ አራት ሆሄ የ1,000 ብዜት ቁጥርን በ9 ስናካፍል ውጤቱ ስንት ይሆናል?

**መፍትሔ፡-**

ትልቁ ባለ አራት ሆሄ ቁጥር = 9000
አካፋይ = 9
ድርሻ = ትልቁ ባለ አራት ሆሄ ቁጥር ÷9
= 9,000 ÷9
=(9× 1,000) ÷9
= 1,000 × (9 ÷ 9)
= 1 × 1,000
= 1,000 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 3

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 7,000 ÷ 5 | መ. 8,000 ÷ 4
ለ. 3,000 ÷ 3 | ሠ. 9,000 ÷ 6
ሐ. 5,000 ÷ 5 | ረ. 10,000 ÷ 8

### 3.2.2.2 እስከ 10,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በ10 ማካፈል

**ተግባር 4፡-**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በ10 አካፍሉ፡፡

   ሀ. 2,000 ÷ 10 ለ. 3,000 ÷10 ሐ. 5,000 ÷10 መ. 7,000 ÷ 10

2. ትንሹን ባለ አራት ሆሄ እና ትልቁን ባለ አራት ሆሄ ቁጥሮች በ10 ስናካፍል ድርሻው ስንት ነው?

**ማስታወሻ**

- የ1,000 ብዜት የሆነን ቁጥር በ10 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው፡፡ በማካፈል የሚገኘው ውጤት በማባዛት ይረጋገጣል፡፡

**ምሳሌ 5** ፡- የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አስሉ፡፡

ሀ. 8,000 ÷10 ለ. 7,000 ÷10

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 8,000÷ 10 =800 ምክንያቱም የ1,000 ብዜትን በ10 በምናካፍልበት ጊዜ የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኝ ቁጥር ስለሆነ

**ማረጋገጫ** 8,000 = 10×800

ለ. 7,000÷ 10 = 700 ምክንያቱም የ1000 ብዜትን በ10 በምናካፍልበት ጊዜ የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኝ ቁጥር ስለሆነ

**ማረጋገጫ** 10×700=7,000

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## መልመጃ 4

1. የሚከተሉትን አካፍሉ

ሀ. 1,000 ÷ 10 ሐ. 4,000 ÷ 10 ሠ. 9,000 ÷ 10

ለ. 5,000 ÷ 10 መ. 6,000 ÷10 ረ. 10,000 ÷10

2. አንድ የግል መድሀኒት ቤት 5,000 ሊትር የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር ለአስር ክፍለከተማ እኩል ቢያከፋፍል እያንዳንዱ ክ/ከተማ ስንት ሊትር የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር ይደርሳቸዋል?

### 3.2.3 እስከ 100,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄና እና በ10 ማካፈል

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት**

- እስከ 100,000 ያሉየ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ማካፈል

### 3.2.3.1 እስከ 100,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በባለ 1 ሆሄ ማካፈል

**ተግባር 5**

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 20,000÷5 ለ. 30,000÷6 ሐ.50,000÷2 መ. 90,000÷3

2. አንድ የለስላሳ ፋብሪካ በ5 ቀናት ውስጥ 90,000 ለስላሳዎችን ያመርታል፡ ፡ ፋብሪካው በአንድ ቀን ምን ያህል ለስላሳዎችን ያመርታል?

**ምሳሌ 6** ፡-የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 1,000 ÷ 2 ለ. 36,000 ÷ 4 ሐ. 60,000 ÷5 መ. 80,000 ÷ 8

**መፍትሔ፡-**

ሀ. $1,000 \div 2 = (100 \times 10) \div 2 = 100 \times (10 \div 2) = 100 \times 5 = 500$

ሐ. $60,000 \div 5 = (6000 \times 10) \div 5 = 6000 \times (10 \div 5) = 6000 \times 2 = 12,000$

ለ. $36,000 \div 4 = (36 \times 1000) \div 4 = 1,000 \times (36 \div 4) = 1,000 \times 9 = 9,000$

መ. $80,000 \div 8 = (8 \times 10,000) \div 8 = 10,000 \times (8 \div 8) = 10,000 \times 1 = 10,000$

## መልመጃ 5

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ።

ሀ. 20,000 ÷ 2　　መ. 45,000 ÷ 5　　ሰ. 56,000 ÷ 8

ለ. 33,000 ÷ 3　　ሠ. 48,000 ÷6　　ሸ. 72,000 ÷9

ሐ. 40,000 ÷ 4　　ረ. 49,000 ÷ 7　　ቀ. 100,000÷8

2. አንድ የችግኝ ጣቢያ 90,000 ችግኞችን አዘጋጅቶ ለ6 አርሶ አደሮች በስጦታ እኩል ቢያከፋፍላቸው ለእያንዳንዱ ስንት ችግኞች ይደርሳቸዋል?

### 3.2.3.2 እስከ 100,000 ያሉ የ1,000 ብዜቶችን በ10 ማካፈል

**ተግባር 6**

1. ትልቁና ትንሹ ባለ አምስት ሆሄ የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ስንት ነው? መልሱን ከአገኛችሁ በኋላ ለአስር አካፍሉ።

2. የሚከተሉትን አካፍሉ

ሀ. 20,000 ÷10　ለ. 24,000 ÷10　ሐ. 50,000 ÷10　መ. 99,000 ÷ 10

**ማስታወሻ**

- የ1,000 ብዜቶች የሚባሉት ቢያንስ የአንድ ቤታቸው፣ የአስር ቤታቸው፣ የመቶ ቤታቸው ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ናቸው።
- የ1,000 ብዜቶች በ10 ስናካፍል ድርሻው የሚገኘው የአንድ ቤት ዜሮን በመተው ነው።

**ምሳሌ 7 :-**

1.የሚከተሉትን የ1000 ብዜቶችን በ10 አካፍሉ።

ሀ. 10000 ÷10　ለ. 36,000 ÷10　ሐ. 60,000 ÷10　መ. 80,000 ÷ 10

**መፍትሔ:-**

ሀ. 10,000÷ 10 =(1,000× 10) ÷10
= 1,000×(10 ÷10)
= 1,000× 1
= 1,000

ለ. 36,000÷ 10 = (3,600× 10) ÷10
= 3,600×(10 ÷10)
= 3,600×1
= 3,600

ሐ. 60,000÷ 10 =(6,000× 10) ÷10
= 6,000 ×(10 ÷10)
=6,000×1
= 6,000

መ. 80,000=(8,000× 10) ÷ 10
= 8,000 × (10 ÷10)
= 8,000 ×1
= 8,000

**መልመጃ 6**

1. የሚከተሉትን የ1000 ብዜቶችን በ10 አካፍሉ።

ሀ. 20,000÷10 መ. 45,000 ÷10 ሰ. 72,000 ÷ 10

ለ. 33,000÷10 ሠ. 48,000 ÷ 10 ሸ. 100,000 ÷10

ሐ. 40,000 ÷10 ረ. 56,000 ÷10 ቀ. 49,000 ÷ 10

2. አስር የእህል ነጋዴዎች አንድ ላይ ተደራጅተው 60,000 ኩንታል እህል ገዝተው እኩል ቢከፋፈሉ እያንደንዳቸው ስንት ይደርሳችዋል?

### 3.2.4 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄና እና በ10 በቀሪና ያለ ቀሪ ማካፈል

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄና እና በ10 ማካፈል

### 3.2.4.1 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 ያለ ቀሪ ማካፈል

**ተግባር 7**

1.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ።

ሀ. 3,636 ÷3 ሐ. 444,000 ÷ 8 ሠ. 72,800 ÷10

ለ. 64,324÷4 መ. 5,670 ÷10 ረ. 1,000,000 ÷ 10

**ምሳሌ 8**

**1.** ረጅሙን የማካፈል ስልት በመጠቀም አካፍሉ።

ሀ. 83,636÷2 ለ. 600,000 ÷ 8

EDUCATION

**መፍትሔ፡-**

ሀ.

```
           41818 (ድ)
(አ) 2 | 83,636 (ተካፋይ)
        - 8
          3
        - 2
          16
        -16
          3
          2
          16
          16
          0
```

ለ.

```
           7 5, 0 00 (ድርሻ)
አ(8) | 600,000(ተካፋይ)
       -56
        40
       - 40
         0
        -0
         0
        - 0
         0
        - 0
         0
```

## ማስታወሻ

➢ የአንድ ቤታቸው 0 የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለአስር ያለቀሪ ይካፈላሉ፡፡ ውጤታቸውም በአንድ ቤት የሚገኘውን ዜሮ በመተው ነው፡፡

**ምሳሌ 9፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 45,670÷10 ለ. 347,580÷10

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 45,670÷10 =4,567 ምክንያቱም የአንድ ቤት ዋጋ 0ሲሆን በምናካፍልበት ጊዜ የአንድ ቤት 0 መተው ነው፡፡

ለ. 347,580÷10 = 34,758 ምክንያቱም የአንድ ቤት ዋጋ 0 ሲሆን በምናካፍልበት ጊዜ የአንድ ቤት 0 መተው ነው፡፡

**ምሳሌ 10፡-** የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 6, 825 ÷ 5 ለ. 89,480 ÷ 8

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

**መፍትሔ፡- ሀ**

| ÷ | 1 | 3 | 6 | 5 | ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | 6 | 8 | 2 | 5 | ተካፋይ |
| | − 5 | 18 − | 32 − | 25 − | |
| | 1 | 15 | 30 | 25 | |
| | | 3 | 2 | ቀሪ 0 | |

ስለዚህ 6,825 ÷ 5 = 1,365 ይሆናል፡፡

ለ.

| ÷ | 1 | 1 | 1 | 8 | 5 | ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | 8 | 9 | 4 | 8 | 0 | ተካፋይ |
| | − 8 | 9 − | 14 − | 68 − | 40 − | |
| | 0 | 8 | 8 | 64 | 40 | |
| | | 1 | 6 | 4 | ቀሪ 0 | |

ስለዚህ 89,480 ÷ 8 = 11,185 ይሆናል፡፡

## መልመጃ 7

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 3,636 ÷ 4 ሐ. 888,000 ÷ 8 ሠ. 672,800 ÷ 10

ለ.109,272÷ 6 መ. 65,670 ÷10 ረ. 1,000,000 ÷10

2. ሶስት ወንድማማቾች ጠንክረው በመስራት በጋራ በ300,000 ብር መኪና ገዝተው ኑሮአቸውን በማሻሻል ላይ ይገኛሉ፡፡ መኪናውን ለመግዛት እኩል ቢያዋጡ እያንዳንዳቸው ስንት ብር ያዋጣሉ?

### 3.2.4.2 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 1 ሆሄ እና በ10 በቀሪ ማካፈል

**ተግባር 8**

1. በ10 ስናካፈላቸው ቀሪ የሚኖራቸው ምን አይነት ቁጥሮች ናቸው? በቡድናችሁ ተወያዩ፡፡
2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ድርሻቸውንና ቀሪውን ፈልጉ፡፡

   ሀ. 476 ÷ 3  ለ. 6677 ÷10  ሐ. 7685 ÷ 8  መ. 28876 ÷10

**ማስታወሻ**

- በማካፈል የተገኘ ውጤት በማባዛት ይረጋገጣል፡፡
- አንድ ሙሉ ቁጥር በሌላ ሙሉ ቁጥር ሲካፈል ቀሪ የሚኖረው ከሆነ የሚረጋገጠው መጀመሪያ አካፋዩን በድርሻ አባዝተን ቀሪውን በመደመር ነው፡፡

**ምሳሌ 11፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች ድርሻቸውንና ቀሪውን ፈልጉ፡፡

ሀ. 3637 ÷3  ለ. 64,923 ÷ 8

**መፍትሔ፡-**

ሀ. 1212 (ድ)
(አ) 3 | 3,637 (ተካፋይ)
- 3
6
- 6
3
-3
7
- 6
1 ቀሪ

ለ. 8115(ድርሻ)
አ(8) | 64,923(ተካፋይ)
-64
9
- 8
12
-8
43
- 40
3 (ቀሪ)

ለማረጋገጥ መጀመሪያ አካፋዩን በድርሻዉ አብዝተን ቀሪውን እንደምርበታለን፡፡
ማረጋገጫ፡ ተካፍይ = (አካፋይ×ድረሻ) + ቀሪ

### መልመጃ 8

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 3,687 ÷ 4   ሐ. 36,377 ÷ 3   ሠ. 8,677 ÷10   ሰ. 56,779 ÷10

ለ. 64,923 ÷ 5   መ. 564,923 ÷ 8   ረ. 44,877 ÷10   ሸ. 725,879 ÷10

2. በአንድ ወረዳ 9,400 ኮምፒዉተሮችን ተማሪዎች እንዲጠቀሙባቸው ለ7 ትምህርት ቤቶች ቢከፋፈሉ ድርሻውን እና ቀሪውን ፈልጉ፡፡

## 3.2.5 እስከ 1,000,000 ያሉ ሙሉ ቁጥሮችን በባለ 2 እና በላይ ሆሄያት ማካፈል

**ተግባር** 9:-

1.የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 3,636 ÷18   ለ. 444,000 ÷ 22   ሐ. 643,216÷ 16

**ምሳሌ 12**

1. ረጅሙን የማካፈል ስልት በመጠቀም የሚከተሉትን አካፍሉ፡፡

ሀ. 44,280÷12   ለ. 600,000 ÷ 25

መፍትሄ:-

ሀ
```
       3,690
12 ⟌ 44,280
     −36
       =82
      −72
        =108
        −108
           =0
            =0
```

መፍትሄ:-

ለ
```
       24,000
25 ⟌ 600,000
     −50
     =100
     −100
        =0
        =0
```

### መልመጃ 9

1. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች አካፍሉ፡፡

ሀ. 6,969 ÷ 13   ለ. 888,000 ÷ 80   ሐ. 582,140÷ 65

2.አንድ መሀንዲስ ጠንክሮ በመስራት መኪና በ348,900 ብር ገዝቶ ኑሮውን በማሻሻል ላይ ይገኛል፡፡ መኪናውን ለመግዛት በ60 ወራት ከፍሎ ቢያጠናቅቅ በአንድ ወር ስንት ብር ይከፍላል?

## 3.2.6 ማካፈልን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**የንዑስ ርዕሱ የመማር ብቃት፡-**

- ✓ እስከ 1,000,000 ባሉ ሙሉ ቁጥሮች ላይ ማካፈልን መሰረት ያደረጉ የቃላት ፕሮብሌሞችን መፍታት

**ተግባር** 10:-

ጥንድ ጥንድ በመሆን ከዚህ በታች የቀረበውን ጥያቄ በመወያየት መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አስረዱ።

1. በአንድ መንደር የሚኖሩ ሴቶች በአካባቢያቸው ልዩ ልዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በማከናወን በ3 ሳምንታት 6,540 ብር ገቢ ቢያገኙ በ1 ሳምንት ውስጥ ስንት ብር ያገኛሉ?

**ማስታወሻ**

- ➢ የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ልንከተላቸው የሚገቡ የአሰራር ዘዴዎች፡
  - ✓ ጥያቄውን ደጋግመን ማንበብ እና መረዳት፣
  - ✓ የተሰጠውን እና የሚፈለገውን በአግባቡ መለየት፣
  - ✓ በተሰጠው የቃላት ፕሮብሌሞችን ውስጥ መጠቀም ያለብንን የሂሳብ ስሌት በትክክል መለየትና ማወቅ፣
  - ✓ ጥያቄውን መስራትና መልሱን ማረጋገጥ

**ምሳሌ 13፡-**

1. አንድ ባለ ሀብት ለአራት በጎ አድራጊ ድርጅቶች 80,000 ብር እኩል ቢያከፋፍላቸው እያንዳንዱ በጎ አድራጊ ድርጅት ስንት ብር ይደርሰቸዋል?

**መፍትሔ፡-**

አጠቃላይ ብር = 80,000

በጎ አድራጊ ድርጅቶች ብዛት = 4

ድርሻ = አጠቃላይ ብር ÷ በጎ አድራጊ ድርጅት ብዛት

= 80,000 ÷ 4

= (8 × 10,000) ÷ 4

= 10,000× (8 ÷4)

= 10,000× 2 = 20,000 ብር ይደርሳቸዋል።

Government of ... EDUCATION ...

## መልመጃ 10

የሚከተሉትን የቃላት ፕሮብሌሞች ፍቱ፡፡

1. አንድ አውሮፕላን በውስጡ 270 ሰዎችን ይይዛል፡፡ በአንድ ወንበር ላይ ሶስት ሰዎች ቢቀመጡ አውሮፕላኑ ስንት ወንበሮች ይኖሩታል?
2. 270 የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ለትምህርታዊ ጉብኝት በከተማችን ከሚገኙ ሙዝየም በመኪና ጉዞ አደረጉ፡፡ እያንዳንዱ መኪና 9 ተማሪዎችን ማጓጓዝ ቢችል ሁሉንም ተማሪዎች ለማጓጓዝ ስንት መኪናዎች ያስፈልጋሉ?
3. አንድ በብርቱኳን ፍራፍሬ ምርት ላይ የተሰማራ ገበሬ 528 ብርቱኳኖችን በ10 ፕላስቲኮች በማሸግ ለገበያ ቢያቀርብ ያልታሸጉት ብርቱኳኖች ብዛት ስንት ነው?
4. በከተማችን በተለያዩ ጎዳናዎች በችግር ላይ የሚኖሩ ሰዎችን በማሰባሰብ የስራ ክቡርነትን በመረዳት፣ በተለያዩ ሙያዎችና የስራ ዘርፎች በ3 ዙሮች 36,000 ሰዎችን ለማሰልጠን ቢታቀድ በ1 ዙር ስንት ማሰልጠን ይቻላል?

Government of Addis Ababa
EDUCATION BUREAU

## የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ

- ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ

  ሀ×ለ = መ ማለት ሀ = መ÷ለ, ለ ≠ 0 እውነት ነው።

- ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ
  - ሀ×ለ = ለ×ሀ (የማባዛት የቅይይር ባህሪ)
  - (ሀ×ለ) ×መ = ሀ×(ለ×መ) (የማባዛት የተጣማጅ ባህሪ)
- የቃላት ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ልንከተላቸው የሚገቡ የአሰራር ዘዴዎች፡
  - ✓ ጥያቄውን ደጋግመን ማንበብ እና መረዳት
  - ✓ የተሰጠውን እና የሚፈለገውን በአግባቡ መለየት
  - ✓ በተሰጠው የቃላት ፕሮብሌሞች ውስጥ መጠቀም ያለብንን የሂሳብ ስሌት በትክክል መለየትና ማወቅ
  - ✓ ጥያቄውን መስራትና መልሱን ማረጋገጥ
- ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር በ10 ለማባዛት ተባዥውን ቁጥር በመውሰድ ከተባዥ ቁጥሩ በስተቀኝ መጨረሻ ላይ 0 መጨመር።
  - ማንኛውም ሙሉ ቁጥር በ0 ሲባዛ ውጤቱ 0 ነው።
  - ማንኛውም የ1,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ሀ ን በባለ አንድ ሆሄ ስናበዛ ዜሮ ያልሆኑትን በጥንቃቄ ካባዛን በኋላ ሶስት 0 መጨመር ነው።
  - ማንኛውም የ10,000 ብዜት ሙሉ ቁጥር ሀ ን በባለ አንድ ሆሄ ስናበዛ 0 ያልሆኑትን በጥንቃቄ ካባዛን በኋላ አራት 0 መጨመር ነው፡
  - የ10,000 ብዜት የሆነ ሙሉ ቁጥር ሁሉ የ1,000 ብዜት ይሆናል።
- ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሀ፣ ለ እና መ , ሀ ÷ ለ = መ, ለ ≠ 0 ማለት ሀ=መ×ለ እና 0 ÷ለ= 0 እና ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ለ 0 ማካፈል አይቻልም የሚሉት ምንግዜም እውነት ናቸው።
- የመቶ ብዜት የሆነን ቁጥር ለ10 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው።
- የ1,000 ብዜትን የሆነን ቁጥር በ10 በማካፈል የሚገኘው ውጤት የቁጥሩን የ1 ቤት ሆሄ 0 በመተው የሚገኘው ቁጥር ነው።

Government of Addis ... EDUCATION ...

- የአንድ ቤታቸው 0 የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለአስር ያለቀሪ ይካፈላሉ። ውጤታቸውም በአንድ ቤት የሚገኘውን ዜሮ በመተው ይገኛል።
- የአንድ ቤታቸው 0 ያልሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለአስር ያለቀሪ አይካፈሉም።
- ያለ ቀሪ የሚካፈሉትን ቁጥሮች ለማረጋገጥ፡ ተካፋይ = አካፋይ × በደርሻ
- በቀሪ የሚካፈሉትን ቁጥሮች ለማረጋገጥ፡ ተካፋይ =አካፋይ × በደርሻ + ቀሪ

Government of Addis Ababa EDUCATION BUREAU

## የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ መልመጃ

1. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ዓ.ነገሩ ትክክል ከሆነ "እውነት" ትክክል ካልሆነ ከሆነ "ሀሰት" በማለት መልሱ

   I. ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር በ0 ሲባዛ ብዜቱ እራሱ ቁጥሩ ይሆናል።

   II. ማንኛውንም ከ0 የተለየ ሙሉ ቁጥር በ10 ለማባዛት በተሰጠዉ ቁጥር

   III. በስተቀኝ መጨረሻ ላይ ዜሮ መጨመር ነዉ።

   IV. ማባዛት በሙሉ ቁጥሮች ላይ የቅይይር ባህሪ የለዉም።

   V. ማባዛት በሙሉ ቁጥሮች ላይ የተጣማጅ ባህሪ አለዉ።

   VI. ማንኛውንም ሙሉ ቁጥር ለዜሮ ማካፈል ይቻላል።

   VII. ዜሮ ለማንኛውም ሙሉ ቁጥር ሲካፈል ድርሻው 0 ነው።

   VIII. ማካፈል በሙሉ ቁጥሮች ላይ የቅይይርም ሆነ የተጣማጅ ባህሪ የለውም።

   IX. የ1 ቤት ሆሄ ዜሮ የሆኑ ሙሉ ቁጥሮች ለ10 ያለ ቀሪ ይካፈላሉ።

   X. ማንኛውም ሙሉ ቁጥር ለባለ 1 ሆሄ ሙሉ ቁጥሮች ይካፈላል።

2. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በ10 አባዙ

   ሀ. 3,615 × 10    ሐ. 38,250 × 10    ሠ. 65,489× 10

   ለ. 100,000 × 10    መ. 98,000 × 10    ረ. 85,300 × 10

3. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮች በባለ አንድ ሆሄ አባዙ

   ሀ. 77,312× 5    ለ. 64,613× 6    ሐ. 100,135×8    መ. 303,275 × 3

4. የሚከተሉትን ጥያቄዎች አባዙ

   ሀ. 4× (10× 9)    ለ. (7×26) ×8    ሐ. (6×3,211) ×2    መ. 10× (3,471×10)

5. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱን ምቹ ለማድረግ እና የተማሪዎችን ውጤት ለማሻሻል የሚያግዙ ስምንት የተለያዩ ክበቦች አሉ። በእያንዳንዱ ክበብ ውስጥ አምሳ አራት ተማሪዎች በንቃት ይሳተፋሉ። ለክበቦቹ ማጠናከሪያ እያንዳንዱ የክበብ አባል 25 ብር ለ10 ወራት ቢያዋጡ፡-

   ሀ. በት/ቤቱ የክበብ አባል የሆኑ ተማሪዎች ብዛት ስንት ነው?

   ለ. በአጠቃላይ ለ8ቱ ክበቦች በ10 ወራት የተዋጣው የገንዘብ መጠን ስንት ብር ነው?

City Government of Addis Ababa
EDUCATION BUREAU

6. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮችን በባለ አንድ ሆሄ አካፍሉ

ሀ. 100 ÷ 4
ለ. 800 ÷ 8
ሐ. 8000 ÷ 6
መ. 9000÷ 7
ሠ. 10,000 ÷ 4
ረ. 40,000 ÷ 8
ሰ. 63,786 ÷ 6
ሸ .800,000 ÷ 9

7. የሚከተሉትን ሙሉ ቁጥሮችን በ 10 አካፍሉ

ሀ. 600 ÷10
ለ. 1000 ÷10
ሐ. 55,760 ÷10
መ. 64,789 ÷10
ሠ. 88674÷ 10
ረ. 995673÷ 10

8. አንድ የሸማቾች ማህበር ለ 8 አርሶ አደሮች 80 ዶሮዎችን እኩል ቢያከፋፍላቸውስንት ይደርሳቸዋል?

9. አንድ መምህር 640 መፅሀፍትን በ8 መደርደሪያዎች ለተማሪ ንባብ እንዲያመቹ አድርጎ ቢደረድር በስንት መደርደሪያዎች ማስቀመጥ ይችላል?

10. በአንድ ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ስር ባሉ ትምህርት ቤቶች በ45 ሳምንቶች የስፖርት ትምህርት ስልጠና የተከታተሉ 390,600 ተማሪዎች ቢሆኑ በአንድ ሳምንት ስንት ተማሪዎች ሰለጠኑ?

11. ህብረተሰብ ክፍሎችን ለመርዳት በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች 18,450,208 ብር በ124 ቀናት ውስጥ ቢያዋጡ በአንድ ቀን ስንት ብር ያዋጣሉ?

EDUCATION BUREAU